
# ትንሣኤ

የዓለም አብያተ ክርስቲያናት
ማኅበር ማዕከላዊ ኮሚቴ
ስብሰባ በኢትዮጵያ

የቤተ ክርስቲያኗ ራስ



የዓለም አብያተ ክርስቲያናት

የቤተ ክርስቲያን ትንሣኤ

የአብያተ ክርስቲያናት አንድነት

የትንሣኤ በዓል አከባበር

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን
በተቀዳሚ ማድረግ የሚገባት

በመንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ሥር የሚካሄድ
የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ሐዋርያዊ ድርጅት

# ማ ው ጫ ።


ገጽ

፩/ መቅድም . . . . . . . . . . . . . . . . . . ፫

፪/ የቤተ ክርስቲያን ራስ . . . . . . . . . . . . ፯

፫/ የቤተ ክርስቲያን ትንሣኤ . . . . . . . . . . . ፲፪

፬/ የትንሣኤ በዓል አከባበር . . . . . . . . . . . ፲፯

፭/ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በተቀዳሚ ማድረግ የሚገባት . . ፳፯

፮/ የአብያተ ክርስቲያናት አንድነት . . . . . . . . . ፴፮

፯/ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር አመሠራረትና ዓላማው ፵፪

፰/ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር ማዕከላዊ ኮሚቴ ስብሰባ
በኢትዮጵያ ። . . . . . . . . . . . . . . . . ፶፩


1963 9.90 ?

# መ ቅ ድ ም

ዘመን አልፎ ዘመን ሲተካ ፤ አንድ ነገር ተረስቶና ወድቆ የነበር እንደገና ሲነሣ ፤ የፈረሰ ሲሠራ ፤ የጠፋ ሲገኝ ፤ ሌላም ይኸን የመሰለ ነገር ሲመለስ ፤ ሲከለስ ለዚያ ነገር ትንሣኤው ነው ። ስለዚህ በዚህ መጽሔታችን ብዙ የተረሱ የቤተ ክርስቲያን ባህሎች ሲወሱ ትንሣኤ ነው ። ስለዚህ አሁን የታደሱትን ሥርዓቶች በየጊዜው ለመጻፍና ለሕዝብ ለማስታወስ ስላሰብን ፤ የዚህን ዜና ማብሠሪያ መጽሔታችን ትንሣኤ ብለን ሰይመነዋል ። ከዚህም ጋር በዚህ ዓመት በሰላም የተፈጸመውን የቤተ ክርስቲያናችን ትንሣኤ የሆነውን ሢመተ ፓትሪያርክ አጉልተን ጽፈንበታል ። የክርስቶስ ትንሣኤ አከባበር በየሀገሩ እንዴት እንደሆነ ከሙሉ በከፊሉ ዘርዝረን አቅርበንበታል ። ይኸን የመሰለው ሌላው ሁሉ ሲገለጥ አንድ የሕይወትና የክብር ትንሣኤ እንደሆነ በመገመት ትንሣኤ ብለነዋል ። ምንም ቤተ ክርስቲያናችን ለሥነ ጽሑፍ እንግዳ ባትሆን ፤ እንደዚህ አድርጎ በመጽሔት መልክ ቤተ ክርስቲያን ነክ የሆኑትን ቁም ነገሮች አዘጋጅቶ ማቅረብ እንደ አዲስ ነገር የቤተ ክርስቲያን ትንሣኤ በመሆኑ ፤ የቤተ ክርስቲያን ትንሣኤ እንደሆነ አምነን ትንሣኤ ብለን እንገምታለን ። እንዲያውም ለክርስቲያን ሕዝባችን እንግዳ የሆነ የዓለም አብያተ ክርስቲያናትን ማኅበር ዓላማና አመሠራረት ፤ የኢስተርንና የኦሪየንታል ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የግንኙነት ጥናት የመጨረሻ ግባቸውንም ሰፋ አድርገን ጽፈንበታል ። ይኸውም አንድ የቤተ ክርስቲያን ትንሣኤ ነው ብለን እናምናለን ።

በዚህ ሁሉ ምክንያት ከዚህ ቀደም ትንሣኤ በማለት ያሳተምናቸው መጽሔቶች ብዙ ሁነው በዕድሜም ዓመቱ ቢሆን ፤---ይኸ የዛሬው ስም ግን ተገቢውን ቦታ ያገኘና ተስማሚ ስለሆነ ፤ የአንባቢዎችን አስተያየት እንደሚማርክ እንተማመናለን ።

# የቤተ ክርስቲያን ራስ

ቤተ ክርስቲያንን በደሙ የቀደሳት ራሱም መሠረት ሁኖ የመሠረታት ኢየሱስ ክርስቶስ ሲሆን ፤ እርሱው የቤተ ክርስቲያን ራስ ነው ። በዚህም አንፃር ለቤተ ክርስቲያንና ለሕዝቡ ደኅንነት የሚያስበው ፣ ቅን ፍርድን የሚፈርደው የእግዚአብሔር እንደራሴ የሆነው ንጉሥ ፣ በየሀገሩ የቤተ ክርስቲያን ራስ ነው ። የቤተ ክርስቲያንም ራስ የበላይም ጠባቂ ተከባካቢ ሆኖ ለቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ልክ መልክ እንዲኖረው ያደርጋል ። እንዲህም አድርጎ የሚሠራው ፤ የሚያስበው ፤ የሚናገረው ንጉሥ ሁሉ ፤ የቤተ ክርስቲያን ራስ ይባላል ።

በሃይማኖቱ ከክርስትና እምነት ውጭ እንኳን ቢሆን ነገሥታቱ የሃይማኖት መሪዎች የሥነ ሥርዓቱም አስከባሪዎች ናቸው ። እንዲያውም ከሌሎች ዓለማት ይልቅ ይኸ ሁኔታ በሚገባ ሲፈጸም የኖረው በኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥትና ቤተ ክርስቲያን ዘንድ ነው ። ምክንያቱም ንጉሠ ነገሥቱ የቤተ ክርስቲያን የበላይ ራስ ሆኖ መንፈሳዊ ተልእኮን ሲፈጽም ፤ ሲያስፈጽም ፤ እንዲሁም ከሕገ ቤተ ክርስቲያን ውጪ ለሆኑት ሲፈርድ ፤ ሲቀጣ ፤ ሲተችኑሯል ። ለቤተ ክርስቲያን ሀብት መብት ሲሰጥ ፤ ሲደለድል የኖረና አሁንም የሚገኝ ነው ። ክርስትናው በመላ ኢትዮጵያ ሊዳረስ የቻለው በቅዱሳን ነገሥታት በእነ አብርሃ አጽብሐ ትጋት እንደሆነ ታሪክ በሰፊው ሲመሰክር ይገኛል ። ቤተ ክርስቲያናችንም ራሷ የተመሠረተች በነርሱ ጥረት በመሆኑ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ነገሥታት የቤተ ክርስቲያን ራስ የበላይ ጠባቂ በመሆን መልካም ግዳጅን ፈጽመዋል ።

የቤተ ክርስቲያናችን የሕግ መጽሐፍ «ፍትሐ ነገሥት» የሚባለው መንፈሳዊና ሥጋዊ አንቀጾችን ያዘለ ሲሆን ፤ ስሙ የነገሥታት ብቻ ፍትሕ መስሚ እንደሆነ የሚያመለክት መስሎ ይታያል ። ይኸም ነገሥታት የቤተ ክርስቲያን ራስና የበላይ ጠባቂነታቸውን ማጽደቁ እንደሆነ ሁላችን ልንገነዘበው ይገባናል ። በዚህም መሠረት ነገሥታት የቤተ ክርስቲያንን ሕግ ሲያስከብሩ ፤ ለቤተ ክርስቲያን አልታዘዝም የሚለውንም አጥፊውን በሕጉ መሠረት ሲቀጡ ትውፊት እስከ ጊዜያችን ደርሶ ይገኛል ።

ቅዱሳን የኢትዮጵያ ነገሥታት ከአብርሃና ከአጽብሐ ጊዜ ጀምሮ ለቤተ ክርስቲያን የሠሩት ታላላቅ ሥራ ሁሉ ፤ በማታልፈው ቤተ ክርስቲያን ዓምድ ላይ ተጽፎ ሁልጊዜ ሲነበብ ፤ ሲተረጐም ይገኛል ። ዓረፍተ ዘመን እየከለላቸው ዘመናቸው በቅጽበት እንኳን ቢያልፍ የአንድ ቀን ውሏቸውን ለቤተ ክርስቲያን እንደሠሩ የማያብለው ታሪክ ይመሰክርላቸዋል ። ለምሳሌ እንደ አፄ ገላውዴዎስ ያለውን ወጣት ንጉሥና በቶሎ ከሕይወት የተለየውን ያስታወስን እንደሆነ ፤ የማያልፍ ሥራን ሠርቶ መልካም መታሰቢያውን ትቶ እንደ ሔደ እንገነዘባለን ። በተለይ ስለ ቤተ ክርስቲያን የሰጠው ምስክርነት « የገላውዴዎስ እምነት» በመባል የታወቀው መሠረተ ሃይማኖት ፤ የጀሱዊቶች ውሽንፍር የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን በሚያዋክብበት ጊዜ ፤ የቤተ ክርስቲያን ራስ እርሱ እንደሆነ የበላይ ጠባቂነቱን ለመግለጥ ፡ እውነተኛ ምስክርነቱን ለመስጠት ያደረገው የማያልፍ መታሰቢያ ሁኖ ይገኛል ። በሀገር ፍቅር የሄድን እንደ ሆነ ወጣትነቱ የሥራ እንቅፋት ሳይሆንበት የፈጸመው ለሁላችን ትልቅ አስረጂ ሆኖ ይታወሳል ። ሌሎችም በዚህ መልክ ቋሚ ሥራ እየሠሩ እንደሄዱ በዚሁ አንፃር ሁሉንም ልናስታውስ እንችላለን ።

በተለይ በዚህ በኛ ዘመን ሥጋዊ ሥልጣኔ ብቻ እያደገ የሕዝቡን ልቦና እያበዘበዘ ማርኮ በሚወስድበት ጊዜ ፤ በመንፈሳዊ አርበኝነት ታጥቆ በአለህበት ጽና የሚል ሃይማኖታዊ አዋጅ የሚናገር እንደ ቅዱስ ገብርኤልም «ንቁም በበህላዌነ እስከ ንረክቦ ለአምላክነ» በማለት የሽማግሌውንም ፤ የወጣቱንም መንፈስ የሚያጽናና ፤ በመንፈስ ከመድከምና ከመሰበር አድነው ሁሉም መንፈሳዊ ጕዳናውን እንዲራመድ የሚመሩን ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ያለ ዘመናቸውን ሁሉ ለቤተ ክርስቲያን ሥራ ያዋሉት ሲሆን ፤ አሁን የሥራቸው ሁሉ ጉልላት አድርገው የሰጡን ጌራ መዊዕ ብለን ልንሠይመው የሚገባን ሢመተ ፓትርያርክ ነው ። ይኸ በመጨረሻ ጊዜ ያቀዳጁን ጌራ መዊዕ የኢትዮጵያ ነገሥታት ሁሉ የቤተ ክርስቲያናችን መሠረቶች የቤተ ክርስቲያን ጉልላቶች እንደሆኑ የሚያስታውስ ጉልህ ሥዕል ነው ። ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ይኸን ጌራ መዊዕ የምንለውን ሢመተ ፓትርያርክ ያስገኙት ከአልጋ ወራሽነታቸው ጊዜ ጀምሮ ያለማቋረጥ በአደረጉት መንፈሳዊ ትግልና ውጊያ እንደሆነ ስንመለከት ፤ ማንኛውም ሰው ትግሉን ያለማቋረጥ ከእግዚአብሔር እምነት ጋር ከቀጠለ በድል አድራጊነት እንደሚገለጥ የታመነ ማስረጃ



ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ
( የቤተ ክርስቲያናችን ራስና የክርስትና ሃይማኖት ጠባቂ) ።

ይሆናል ። ይኸንም ለመፈጸም ያነሣሣቸው ፍጹም የሆነ የሀገር ፍቅራቸውና
የቤተ ክርስቲያን ራስነት ነው ። የቤተ ክርስቲያን ራስ አሳቢ ፤ ተቆርቋሪ እር
ሳቸው በመሆናቸው ፤ ማንኛውንም ከጠላት የሚሰነዘረውን ፕሮፓጋንዳ
ሳይመለከቱ ሥራቸውን ብቻ በመቀጠል ቢሠሩ ፤ ይኸን የመሰለ ውጤት ሊያስገኙ
ቻሉ ። በዘመን መጨረሻው ጊዜ ደርሰን ኻያኛው መቶ ዘመን ሲሆን ገና ራስን
የመቻል ጥቅምና ጉዳትን ለይቶ የማወቅ ዕድል ያልተሰጣቸው ብዙ ናቸው ። ስለ
ዚህም እውነቱ ሳይገባቸው ኢትዮጵያ ለኢትዮጵያውያን የሚለውን ዘይቤ ሳይ
ረዱና ከንጉሠ ነገሥቱ ሰልፍ ሳይገቡ የቀዩ ብዙዎች ነበሩ ። የጨዋ ልጆች ብቻ
ሳይሆኑ ካህናትም ቢሆኑ በኢትዮጵያ ጳጳስ ላይ ያላቸው እምነት ሌላ ነበር ። እን
ደዚያ ያለው ያለዐዋቂ ጊዜ አልፎ የንጉሠ ነገሥቱ ትግል አቸንፎ ከጳጳስነት
ወደ ፓትሪያርክነት ደረጃ ደርሶ በተለይም በኛው መራጭነት ፤ በኛው ሿሚ
ነት ተፈጽሞ ማየት ፤ የዕድላችን ሁሉ ጉልላት መሆኑን ያስረዳል ። በእርግ
ጥም ንጉሠ ነገሥቱን የቤተ ክርስቲያን ራስ የሚያሰኘውን ሥያሜ ያጸናዋል ። ጌራ
መዊዕም ለቤተ ክርስቲያን የተገባት ሀብት ሲሆን ፤ እያንዳንዱ ምእመን በራሱ
ላይ እንዳለ ዐውቆ የሸክሙ ተካፋይ ለመሆን መሰለፍ አለበት ። ማግኘት
ቀላል ይሆናል ። ከባድ ነገር ቢኖር ያገኘውን መጠበቅና በተገቢው ቦታ
ማዋል ነው ። ስለዚህ ኢትዮጵያውያን የተባልን ሁሉ ኅብረታችንን አጽንተን
ሸክማችንን አቅለን በተሰጠን ጌራ መዊዕ ማጌጥ የቤተ ክርስቲያናችንን ራስ
ማወቅ ተገቢ ነው ።

የቤተ ክርስቲያን ራስ ፤ የቤተ ክርስቲያን ጉልላት የሆኑት ንጉሠ ነገሥታችን
ለቤተ ክርስቲያን እስካሁን የፈጸሙላት ቁም ነገሮች ብዙዎች ሲሆኑ ፤ አሁንም
ለቤተ ክርስቲያን ጌጥ የሚሆነውን ውስጣዊና አፍአዊ አስተዳደር መልክ እንዲስ
ጡላት ደጅ ትጠናለች ። ራስ በልዩ ልዩ ሕዋስ ይጸናል ። ሕዋሳት ደግሞ
በራስ ይንቀሳቀሳሉ ። ሙሉ አካል የሚባለውም ሙሉ ሕዋሱ የሠራ እንደ
ሆነ ነው ። ስለዚህ ራሳችን ዐውቀን በሕዋሳችን ሠርተን የምንጠቀም መሆን
አለብን ። የቤተ ክርስቲያን ራስ ሙሉ ጤና ኑሮት ብዙ የሠራውን ያህል ውስ
ጣዊና አፍአዊ አካልም ሙሉ ጤንነት ኑሮት የሚፈለግበትን ቁም ነገር
ፈጽሞ ለመታየት የሚጓጓው ብዙ ነው ።

ሊቀ ሥልጣናት ሀብተ ማርያም ወርቅነህ ።

# የቤተ ክርስቲያን ትንሣኤ

ቤተ ክርስቲያን የማትሞት ፤ የማታልፍ ቋሚ ሐውልት መሆኗ እንደ ሃይማኖታዊ ውሳኔ የሚነገርና የሚታመን ነው ። ግን በውስጥ አሠራሯ የደከመች በውጪ ወራሪ የተዘረፈች እንደሆነ ሞተች እንኳን ባትባል ፤ ወደቀች መባሏ አይቀርም ። አንድ ጊዜ በዚህ መልክ ከወደቀች ደግሞ ፤ ወድቃ የምትቀር ትሆናለች ። ዕድል ገጥሟት የምትነሣ እንዳለች ግን የግድ የቤተ ክርስቲያን ትንሣኤ ተብላ ትጠራለች ። በመሠረተ ሃይማኖት የማትሞት ቤተ ክርስቲያን የጸ ትባለው ፤ አንድ እምነት ፤ አንድ ሥርዓት ያላቸው የምእመናን አስተሳሰብ ኖሯት አንድ ሲሆን ነው ። ምዕመናኑ ከተለያዩ ፤ ሥነ ሥርዓቱም ካልተጠበቀ አዲስ የሥራ እንቅስቃሴ ተፈጥሮ ለቤተ ክርስቲያን አዲስ መሥመር ስለማይከፈት ፤ ቤተ ክርስቲያን ትወድቃለች ። መውደቅም ብቻ ሳይሆን ትሞታለች ። ምውት ቤተ ክርስቲያን እየተባሉ የሚጠሩ እንደ ኩሬ ውኃም የማይንቀሳቀሱና አዲስ ሕይወት ያለው ነገር በውስጣቸው የማይገኝባቸው በብዙ አህጉር ይገኛሉ ▪ ከነዚያም ውስጥ ለአንዳንዶች ዕድል ገጥሟቸው ከተቀበሩበት ሲነሡ ፤ ትንሣኤ አገኙ ይባላሉ ። ቤተ ክርስቲያን ሕይወት አግኝታ ተነሣች ፤ ተንሠራራች እየተባለ ይነገራል ።

አንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን የራሱን ባህል ብቻ በመጠበቅ ከማንም ርዳታ ሳይጠይቅ ወድቆ በመፈራገጥ ዘመኑን ይፈጽማል ። ይህም ሊሆን የሚችለው ፤ አንዱ ቤተ ክርስቲያን ከሌላው አብያተ ክርስቲያናት ርዳታ መጠየቅ ውርደት እየመሰላት ነው ። በመንግሥት በኩል የሔድን እንደሆነ ፤ እያንዳንዱ መንግሥት በሌላው መንግሥት እየተረዳ ልክ ሌላው ከደረሰበት ለመድረስ ሲንጠራራ ይገኛል ። ስለዚህም ወደኋላ የቀሩት አገሮች የሚለውን ቃል አስለውጠው በመልማት ፤ (በማደግ) ላይ ያሉት አገሮች እየተባሉ ይነገርላቸዋል ። ቤተ ክርስቲያንም በልዩ ልዩ መስክ ተሠማርታ መሥራትና በችግሯ ፈጥነው የሚደርሱላት ወዳጆች ማበጀት ፤ እንዲሁም ርዳታ መጠየቅ ሲገባት በየሀገሩ በቍጥር ያነሱ ፤ በሥራ ወደኋላ የቀሩ አብያተ ክርስቲያናት በብዛት ይገኛሉ ። ከዚህ ሌላ አንዱ ቤተ ክርስቲያን ሌላውን መጨቆን ፤ እንዳይታወቅም ማድረግ ፡ ስሙንም ማጥፋት ፤ በአደባባይም እንዳይውል ማድረግ

የሚወዱ አብያተ ክርስቲያናት ይገኛሉ ። ይኸን የመሰለው መጥፎ ዕድል ቢ
ክርስቲያናችንን ገጥሟት ብዙ ጊዜ ስሟን ለውጠው ኮፕቲክ ቸርች (የግብ
ቤተ ክርስቲያን) እየተባለች ስትጠራ ፤ በተጠያቂነትም እነርሱ እየቀረቡ አ
ረጅ እየሆኑ የሠሩበት ጊዜ ረጅም ነው ። በአንዳንድ ቦታ ላይ ለምሳሌ እን
ኢየሩሳሌም ባለው ገዳም በእጀ መናኛ እየገቡ ባለቤት መሆን የጀመሩበ
ጊዜ ረጅም ሲሆን ፤ ቤተ ክርስቲያናችን ራሷን ለመቻል ፤ ከጽዕለት ለመዳ
ያደረገችው ጥረት ብዙ ነው ። ይኸን ተጽዕኖ አልፎ ራስን ችሎ መገኘ
አንድ ትንሣኤ ነው ። ስለዚህ የቤተ ክርስቲያን ትንሣኤ ከቀዳማዊ ኃይ
ሥላሴ ዘመነ መንግሥት ጀምሮ ነው ለማለት እንደፍራለን ። ቤተ ክርስቲያ
ማለት የራሱ የሃይማኖት ውሳኔ ኑሮት በዚያ ሲመራና ሲያስተምር ፤ የራሱ
ሕገ ቤተ ክርስቲያን ኑሮት በዚያ ሲመራ ፤ የራሱ መሪ ኑሮት በዚያ ጽላሎ
ረድኤት ሲጠበቅና ሲመራ ነው ።

ምንም ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት የሾምንበት ጊዜ ቀደም ያለ ሁኖ እርሱ
አንድ የትንሣኤ ምልክት ሁኖ ትንሣኤ ቢባል ፤ ራሱን ፓትሪያርክነቱ
በእኛው ሿሚነት ፤ በኛው መራጭነት ስንፈጽም እውነተኛው የቤተ ክርስቲ
ያን ትንሣኤ ነው ።

ቤተ ክርስቲያናችን ጥንታዊት ስትሆን ዜማዋ ፤ ሥነ ሥርዓቷ ፤ ቋንቋዋ
ሌላም ይኸን የመሳሰለው ራሱን የቻለ ሲሆን ፤ ጳጳሱ ብቻ የውጪ አገር ሰው
በመሆኑ ቤተ ክርስቲያን ተጥላ ወድቃ እንደኖረች የሚያስገምት ነው ። ጥን
ታውያን ጳጳሳት ከውጪ አገር ሲመጡ ፤ ዕውቀታቸው በመጠኑ ይሁን
እንጂ ፤ ዓለም የት እንደደረሰ ያውቁ ነበር ። የቀረው ቀርቶ የነርሱም ቤተ
ክርስቲያን ቢሆን በመጠኑ የተሻለ አስተዳደር ሲኖረው ፤ ለኛ ግን የወሰኑት
የጸፉት አንድም ነገር አልተገኘም ። ቤተ ክርስቲያናችን ናት ይኸ ይገባታል
ይኸ ያስፈልጋታል ብለው ያቆዩልን አንድም ቋሚ ነገር የለም ። በእርግጥ
ቤተ ክርስቲያናችን አልሞተችም ብለን አንዋሽም ። ግን ተባርዮ የማያስቀ
ረው አምላክ ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን አሥነሥቶ ቤተ ክርስቲያናችንን
ከውድቀት አሥነሣት ። ራሱን የቻለ አስተዳደር እንዲኖራት ኢትዮጵያውያን
ጳጳሳት እንዲባርኳት አደረጉ ። ይኸ አንድ ትልቅ ትንሣኤ ሁኖ ስናከብረው ፤
ፍጹም የቤተ ክርስቲያናችን ትንሣኤ ይሆን ዘንድ በፓትሪያርክነት ደረጃ እን
ድትገኝ ያደረጉት በተጨማሪ የቤተ ክርስቲያናችን ፍጹም ትንሣኤን የሚሰ
ብክ ነው ።





ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ወፓትሪያርክ ዘኢትዮጵያ

እንግዲህ የቤተ ክርስቲያን ትንሣኤ ብለን በያመቱ ስናከብር ፤ «እንከሰ ኢንረድ ታሕተ» እያለች በምንም መልክ የበታችነት ሳይታይባት ቤተ ክርስቲያን ከሁሉ ጋር ተካክላ ተግባሯን ታከናውናለች ማለት ነው ።

ለዚህ ለአዲሱ የቤተ ክርስቲያን ትንሣኤ አከባበርና ለአዲሱ የቤተ ክርስቲያን የሥራ አመራር ተስማሚ ሆነው የተገኙ ፤ ፓትረያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ናቸው ። እርሳቸውንም ለዚህ የምርጫ ዕድል ያበቃ አምላክ ቤተ ክርስቲያናችን በተገቢው መሥመር እንድትራመድ ያደርጉ ዘንድና አምላክ ይረዳቸው ዘንድ እንጸልያለን ።

ክርስቲያኑ ሕዝባችን በመላ የተቀበለውን ይኽን ምርጫና ሢመት የቤተ ክርስቲያን ትንሣኤ ብለን ስንሰይመው ፤ ቀደም ብሎ በቤተ ክርስቲያን ላይ ምን ያህል ድቀት እንደነበረባት በጉልህ የሚያሳይ መነጥር ነው ። ይሁን እንጂ ወድቆም የተነሣ ፤ ሙቶም የተነሣ ቢሆን ፤ ለጋ መሆኑና ሊራመድ የማይቻለው መሆኑ እርግጠኛ ነገር ነው ። ይኽም ከሆነ የወገን ሁሉ ድጋፍ ያስፈልገዋል ። በዚህ አንፃር ቤተ ክርስቲያናችን ተነሣች ስንል ፤ በኛ በኩል የምሥራች ነው ። በአንድ በኩል ደግሞ ለርዳታ ጥሪ ነው ። ወገን የሆነ የሚታወቀው በርዳታ ሲሳተፍ ነው ። ኢትዮጵያውያን የሆን ሁሉ ፤ ቤተ ክርስቲያንን መርዳት አለብን ። ቤተ ክርስቲያናችን የሃይማኖት መዝገብ ፣ የባህል እናት ፤ የጥበብ ምንጭ ናት ። የኢትዮጵያ ባህል ሁሉ የተወሰደው ከቤተ ክርስቲያን ነው ። ጥበብ ሁሉ የፈለቀው ከቤተ ክርስቲያን ነው ። ይኽም ከሆነ የቤተ ክርስቲያናችን ትንሣኤ ፤ የባህላችን ትንሣኤ ፤ የጥበባችን ትንሣኤ ነው ። የቤተ ክርስቲያናችንን ትንሣኤ በዓሉን እናክብር ፤ ደስታውን እንሳተፍ ።

# የትንሣኤ በዓል አከባበር

ትንሣኤ ማለት ተንሥአ ካለው የግዕዝ ግሥ የተወረሰ ሲሆን ፤ የቃሉ ...ትም መነሣት አነሣሥ ማለት ነው ። በዘመን አሪት ይከበር የነበረው በዓል ...ካ እሥራኤል ዘሥጋ ከባርነት ቀንበር ወደነፃነት የተላለፉበት ፤ ከኀዘን ... ደስታ የተሸጋገሩበት በዓል ነበር ።

በዓለ ትንሣኤ ደግሞ በዘመን ሐዲስ እሥራኤል ዘነፍስ ወይም ምእመናን ...ጢአት ወደጽድቅ ከሐሳር ወደክብር ፤ ከሰይጣን አገዛዝ ወደዘላለማዊ ነፃ... ፤ ከአሮጌ ሕይወት ወደ አዲስ ሕይወት የተሸጋገሩበት መንፈሳዊ በዓል ... ። በዚህ አኳኋን የትንሣኤን በዓል ክርስቲያኖች ሁሉ በታላቅ ስሜት ስለ...የከብሩት ፤ የትንሣኤ በዓል ታላቅና በዞረ በዓላት ሆነ ። ይህንም የሚያስ... በእኛ ቤተ ክርስቲያን ብቻ ሳይሆን ፤ የምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት እየ...ብሉ የሚጠሩት ሁሉ ከልደቱና ከሌሎቹ በዓላት ይልቅ ፤ የትንሣኤውን በዓል ...ልዩ ናፍቆት የሚጠብቁና የሚያከብሩ በመሆናቸው ነው ። ይህንን ለማገና... ፋሲካ (ፓስኻ) ብለው ሰይመውታል ። ትርጉሙም (ማዕዶት መሸጋገሪያ) ...ለት ነው ።

## የትንሣኤ በዓል አከባበር መቼ ተጀመረ ?

የትንሣኤ በዓል መከበር የተጀመረበትን ዓመተ ምሕረቱንም ሆነ ዕለቱን ...ዲስ ኪዳንም ይህ ነው ብሎ ዕለቱን ለይቶ ባይገልጽም ፤ ጌታችን ኢየሱስ ...ርስቶስ የተነሣበትን እርግጠኛውን ዕለትና ዓመተ ምሕረት መንፈሳውያን ...ታውንትና የታሪክ ሰዎች መጋቢት ፳፱ ቀን ፴፬ ዓ. ም. እንደሆነ ስለትንሣ...ው በጻፉት በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ይገኛል ።

በሌላ በኩል ደግሞ የታሪክ መድበል ወይም ኢንሣይክሎፔድያ የተባ...ው መጽሐፍ ክርስቶስ ስለተነሣበት ዕለትና የት መጣውንም ጭምር በጻፈ...ት እርእስት ላይ ፤ አረማውያን የጌቶች ጌታና የአማልክቶች አምላክ ...ለው ፀሐይን ያመልኩ ነበር ። የሚያከብሩበትም ዕለት እሑድ ሆነ ፤ ካለ

በኋላ ፤ ሊቃውንቱም በዘመኑ የነበሩት ሕዝቦች ቀኑን በለመዱት እንዲያከብ
ሩትና ነገሩም እንግዳ ሁኖ ግራ እንዳያጋባቸው ሲሉ የጌቶች ጌታና የአማል
ክት አምላክ እውነተኛ ፀሐይም የሆነው ክርስቶስ እሑድ ስለተነሣ ፤ የጣዖ
በዓል ይከበርበት በነበረው ዕለት የትንሣኤን በዓል ተክተው እንዲከበር አደ
ረጉ ይላል ። እውነተኛው ምክንያት ግን ክርስቶስ ድል አድርጎ የተነሣበት ነ
ነትን የሰበከበት ዕለት ስለሆነ ፤ እሑድ የነፃነት በዓል ሁኖ ሲከበር ይኖራል።
ምንም እንኳን በዓሉ በአሁኑ ጊዜ በልዩ ልዩ ሥነ ሥርዓትና በደመቀ አኳኋን
በብዙ ዝግጅት ባይከበርም ፤ ያቋረጠበት ጊዜ የለም ። መጀመሪያም በደቀ መዛሙ
ርቱና በሰባ አርድዕት ፤ ኋላም በየጊዜው በሚነሡት ተከታዮች ሲከበር ኖሯል ።

ይሁን እንጂ አከባበሩ ባይቋረጥም በቀን አቈጣጠር በኩል በአብያተ ክር
ስቲያናት መካከል ብዙም ባይሆን ጥቂት ልዩነት እንደነበር ይኸው መጽሐፍ
ያብራራል ። የእስክንድርያና የሮም አብያተ ክርስቲያናት በቀን አቈጣጠር
ረገድ ደኅና ተመራማሪ ሊቃውንቶች ስለነበሩአቸው መጀመሪያም ከነበረው
ከአይሁድ የቀን አቈጣጠር ለየት ብለው የትንሣኤ በዓል ከሚያዝያ ፳፭ እንዳ
ይወጣ ፤ ከመጋቢት ፳፩ በታች እንዳይወርድ ወስነው ነበር ።

ስለዚህ በነዚህ አካባቢ ያሉትን ቀኖች ተከትለው የትንሣኤን በዓል
እያከበሩ ሕዝቡንም እንዲያከብር ያስተምሩት ነበር ። በትንሹ እስያ አካባቢ
የምትገኘው የአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን ግን የአይሁድን የቀን አቈጣጠር
ተከትላ ሚያዝያ ፲፬ ቀን የትንሣኤን በዓል ታከብር ነበር ። በኋላ ደግሞ
በ፫፻፳፭ ዓ. ም. በኒቅያ የተሰበሰበው ጉባኤ የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን አቈ
ጣጠር ከማንኛውም ተሻሽሎና ቀረብ ብሎ ስላገኘው ፤ እሱን አጽድቆ ተለይ
ቷል ሲል ያትታል ። አውግስጢን የተባለው ሊቅ ደግሞ በበኩሉ ፤ የትን
ሣኤ በዓል በፈረንሣይ አገር በ፫፻፹፯ ዓ. ም. ሚያዝያ ፳፩ ቀን ሲከበር ፤ በኢ
ጣልያ አገር ደግሞ በዚሁ ዓመተ ምሕረት ሚያዝያ ፲፰ ፤ በእስክንድርያ ደግሞ
ዓመተ ምሕረቱ አንድ ሁኖ ሚያዝያ ፳፭ ቀን ተከብሯል ሲል በጻፈው መጽ
ሐፉ ገልጾአል ። በ፬፻፶፩ ዓ.ም. በኬልቄዶን ጉባኤ ከተደረገው ልዩነት ወዲህ
ደግሞ ፤ ከ፬፻፶፭—፭፻፳፭ ዓ. ም. በእስክንድርያና በሮም መካከል የሰባት ቀን
ልዩነት ተፈጥሮ የበዓሉ አከባበር በቅደም ተከተል መከበር ጀመረ ይባላል ።
ከዚያን ዘመን ጀምሮ አሁን እስካለንበት ድረስ የምዕራብ አብያተ ክርስቲያ
ናት የትንሣኤን በዓል ሰባት ቀን ቀደም ብለው ሲያከብሩ ፤ የምሥራቅ አብ
ያተ ክርስቲያናት ደግሞ እነሱ ካከበሩ ከሰባት ቀን በኋላ የትንሣኤን በዓል
ያከብራሉ ።



ኢትዮጵያ ግን ቀደም ብላ ሕገ ኦሪትን ተቀብላ ስለነበር እስከ ፫፻፴ ዓ.ም
ድረስ የትንሣኤን በዓል ማክበር እንዳልጀመረች ይገመታል ። ከዚህ በኋላ ግን
አቡነ ሰላማ ከቅዱስ አትናቴዎስ ሢመተ ጵጵስናን ተቀብሎ ሥርዓተ ቤተ ክር
ስቲያንን ከማጥናቱም ሌላ ፤ ቅዱስ አትናቴዎስ በኒቅያ ጉባኤ ስለነበር ስለት
ንሣኤ በዓል አከባበርና የቀን አቈጣጠር ጉባኤው ያጸደቀውን ከሱ ተቀብሎ
ወደ ኢትዮጵያ ይዞ ስለመጣ ፤ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እስካሁን ድረስ የኢትዮጵያ
ኦርቶዶክሳዊት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ይህንኑ የትንሣኤ በዓል ራሷ እያከበ
ረች ፤ ሕዝቡንም ስታስከብር ቆይታለች ። ወደፊትም ስታከብር ትኖራለች ።
ይህም ሊሆን የቻለው ለሐዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን ምሳሌ ሁና በቆየችው
በቀድሞዪቱ ቤተ መቅደስ ከዓመት አንድ ቀን ሊቀ ካህናቱ የሕዝቡንም ሆነ
የራሱን ኃጢአት ለማስተስረይ የኮርማዎችንና የፍየሎችን ደም እየያዘ ወደዚ
ችው ሥፍራ ይገባ ነበር ። (ዕብራውያን ፲ ፥ ፫)

በዚህ አኳኋን መሥዋዕት ሆኖ የሚቀርበውም ልዩ ልዩ እንስሳ ከየአንዳ
ንዱ ምእመን ለኃጢአት ማስተሥረያ ሁኖ የሚሰጥ ስጦታ ነው እንጂ ሊቀ ካህ
ናቱ ከራሱ መሥዋዕት አያቀርብም ነበር ። ከዚህ የተነሣ በዚያን ጊዜ የነበ
ረው ማንኛውም ሰው በሊቀ ካህናቱም ሆነ በቤተ መቅደሷ ላይ ሙሉ እምነ
ቱን አያሳድርም ነበር ። ሊቀ ካህናቱም ቢሆን ለዓለም ራሱን መሥዋዕት አድ
ርጎ ለሚሰጠውና ሙቶም ከተቀበረ በኋላ በሦስተኛው ቀን ለሚነሣው ለእው
ነተኛው ሊቀ ካህናት መግለጫ ምልክት ነበር እንጂ እርሱን የሚወክል አል
ነበረም ።

በዚሁ ዓይነት ምሳሌ እየሆኑ መባዕና መሥዋዕት ይቀርባሉ ። እነዚህም
እስከ አዲሲቱ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን መቋቋም ድረስ የተፈጸሙና ስለም
ግቡና ስለመጠጥም ፤ ስለልዩ ልዩ መንፃትም የሚሆኑ የሥጋ ሥርዓቶች በመ
ሆናቸው መንፈሳዊ ሥርዓትም ስለሌለባቸው የሚያመልከውን ሕዝብ በሕሊና
ፍጹም ሊያደርጉት አልቻሉም ነበር ።

ሆኖም እውነተኛው የፋሲካችን በግ የሆነው ክርስቶስ ይመጣ ዘንድ ላለው
ጊዜ ቀጠሮ ሁነው ቆዩት ። ክርስቶስ ግን ሊቀ ካህናት ሁኖ በመጣ ጊዜ ፤
በመሞቱ የዘለዓለም ቤዛ ሁኖና የሰውን በደል ሁሉ አጥፍቶ በገዛ ደሙ ወደ
ቤተ ክርስቲያን ገባ እንጂ ፤ በፍየሎችና በጥጆች ደም አይደለም ። በማስተሥ
ረያ ቀን በቤተ መቅደስ የሚቀርበው መሥዋዕት በየዓመቱ ሲቀርብ በቅድስት
ቤተ ክርስቲያን መሥዋዕት ሆኖ የሚቀርበው ክርስቶስ ግን ስለዓለም ኃጢ
አት አንድ ጊዜ ቀረበ ። በአሪት ጊዜ የነበረው የእንስሳት መሥዋዕት ግን

ጊዜያዊ ከመሆኑም ሌላ አቅጣጫው የሚያመራው ወደክርስቶስ ብቻ መሆኑ ያመለክተናል ። በዚህ አኳኋን ክርስቶስ በመራራ ሥቃይ አቋርጦ የሞት ጉዳና በኀልጎታ አልፎ የተነሣው ፤ የዘለዓለም ሊቀ ካህናት ለመሆን ነው ።

ስለዚህ የትንሣኤ በዓል በቤተ ክርስቲያን በኩል ታላቅ ሞገስን የሚሰ በመሆኑ ክርስቶስ የተቀበረባት የጎልጎታ ምሳሌ የሆነችው ቤተ ክርስቲያን ከሞት ተነሥቶ ለጠቅላላው ዓለም የሰጠውን ስጦታ በየዓመቱ የትንሣኤው በዓል ራሷ እያከበረች ምእመናንም እንዲያከብሩ ታስተምራለች ።

## የትንሣኤ በዓል አከባበር በኢትዮጵያ ፤ ከቤተ ክርስቲያንና ከካህናትም ሆነ ከሕዝቡ ባህል ጋር ያለው ግንኙነት

፩ኛ/ ቅድስት የተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን በጨለማ የነበራችሁ ሕዝ ቦች ኑ ፤ የትንሣኤውን ብርሃን እዩ ፤ ብርሃኑን ወስዳችሁ የብርሃኑ ተካፋይ ሁኑ እያለች ስታዘጋጅ የሰነበተችውን ጧፍ እያበራች ታድላቸዋለች ። የክርስቶ ንም ሥጋና ደም አዘጋጅታ እንዲቀበሉ ትሰጣቸዋለች ።

ይህንም መሠረት በማድረግ ቀደም ብሎ በነበረው ዘመን ኢየሩሳሌም የሚገኘው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ገዳም አበምኔት ከሌሊቱ ፳ ሰዓት ሲሆ ወደ ክርስቶስ መቃብር ይገባና ይጸልያል ። ወዲያው ከሚበራው ብርሃን ይ ይወጣና በኢየሩሳሌም ለሚገኙት የዓለም አብያተ ክርስቲያናት አለቆች በ ዙት የጧፍ ችቦ ላይ ያበራላቸዋል ። ከዚህ በኋላ በየቤተ ክርስቲያናቸው መ ራታቸውን እያበሩ የትንሣኤውን ደስታ ለክርስቲያኖች ይገልጡ ነበር የሚል ታሪክ ይገኛል ።

ስለዚህ ቤተ ክርስቲያናችን «ትንሣኤህን ላመንን ፤ ብርሃንህን በኛ ላይ ላ ልን » ፤ እያለች ታከብራለች ።

፪ኛ/ ከካህናቱ ጋር ያለው ግንኙነት ፤ ካህናቱ ግብረ ሕማማቱን ሲያነበ ይሰነብቱና ለትንሣኤ አጥቢያ ከሌሊቱ ሁለት ሰዓት ተኩል ሲሆን ፤ ለጸሎት ተሰብሰበው የሚለውን ያወል ይደውላሉ ። ተፈሥሒ ማርያም ፤ ለአዳም ሩ ክሁ የሚለውን የደስታ መዝሙር ይጀምራሉ ። ቀጥሎም ሥርዓተ ቅዳ ከደረሰ በኋላ ዲያቆኑ «ወተንሥአ እግዚአብሔር ከመ ዘንቃሀ እምንዋ ወከመ ኃያል ወኅዳገ ወይን ፤ ወቀተለ ጸሮ በድኅሬሁ » ትርጉሙም እግዚአ



ሔርም ከእንቅልፍ እንደሚነቃ ተነሣ ። የወይን ስካር እንደተወው እንደ ኃያ ልም ሰው ጠላቶቹን በኋላቸው መታ » የሚለውን የዳዊት መዝሙር ፸፯ ቊ. ፷፭ ለመዘመር ብቅ ይላል ።

ለምሳሌ ሁለት መላእክት ነጭ ልብስ ለብሰው በቀኝና በግራ ሁነው በመ ቃብሩ እንደታዩ ሁሉ ፤ ዲያቆኑም ነጭ ልብስ ተክህኖ ለብሶ በእጁ መስቀል ጨብጦ ነጭ ልብስ ተክህኖ በለበሱና የደመቀ መብራት በያዙ ሁለት ዲያቆ ኖች በግራና በቀኝ ታጅቦ ከላይ የተጠቀሰውን ምስባክ በሰበከ ጊዜ ፤ ካህናቱ ከበሮ እየመቱ እሱ ያለውን በመቀበል ይዘምራሉ ፤ ቀጥሎም ቄሱ ስለትንሣ ኤው የሚያበሥር ወንጌል ያነባል ። በመጨረሻም « ዮም ፍሥሐ ኮነ » «ዛሬ ደስታ ሆነ » የሚለውን አንገርጋሪ አንድ ደብተራ መስቀል ይዞ ያመለጥ ናል ። ደብተሮቹም ይዘሙታል ፤ ይጸፋታል ፤ ያሸበሽቡታል ፤ ወዲያውም ትንሣኤህን ለመን ብርሃንህን ላክልን የሚለውን እስመ ለዓለም እየወረቡና መብራት እያበሩ ሁደት ያደርጋሉ ። ከዚያም ሲመለሱ» ይእቲ ማርያም» የተባ ለውን የኪዳን ሰላም ይጸፉና ኪዳን አድርሰው መወድሱን ካዜሙ በኋላ ይዘ ሙታል ። ወዲያው ይትፌሣሕ የሚለውን መዝሙር ከዘመሙ በኋላ ፤» ምድር በክርስቶስ ደም ታጠበች» እያሉ ሲጸነጽሉ ፤ ቄሱ» ክርስቶስ ተንሥአ እሙታን በዓቢይ ኃይል ወሥልጣን አሠሮ ለሰይጣን አግዐዞ ለአዳም ሰላም እምይእዜሰ ይኩን ሰላም » እያለ መስቀል ከማሳለም ጋር እግዚአብሔር ይፍታሕ በማለት ለሕዝቡ ያውጃል ። ጠበልም ይረጫል ፤ መጨረሻም ቅዳሴ ይቀደስና ዕጣን ሞገር ተቋሞ ሠርዋተ ሕዝብ ከሆነ በኋላ ፤ ለመፈሰክ ሁሉም ወደየቤቱ ይሔ ዳል ።

፫ኛ/ ከሕዝቡ ጋር ያለው ግንኙነት ፤ የትንሣኤን በዓል በአምስቱ ክፍለ ዓለማት የሚገኙ ክርስቲያኖች ሁሉ ያከብሩታል ። ይልቁንም የምሥራቅ ክር ስቲያኖች በልዩ ልዩ ሥነ ሥርዓትና ዝግጅት ያከብሩታል ። የበዓሉም አከባ በር የሚፈጸመው ያን ጊዜ በመቃብር የታየውን ደስታ በመከተል ነው ። ይህም ማለት ቅዱሳት አንስት የተቀበረውን የክርስቶስን ሥጋ ሊቀቡ በያ ዙት ሽቱ ፤ ከመቃብሩ ሊያስቀምጡ በወሰዱት አበባ አምሳያና ለስጦታቸው መልስ «ክርስቶስ ተነሥቷል» የሚል የምሥራች ከቅዱሳት መላእክት የተነገራቸ ውን ደስታ መሠረት በማድረግ ነው ።

ስለዚህ የምሥራቅ ክርስቲያኖች የትንሣኤን በዓል የሚያከብሩበት ዕለት አንድ ቢሆን እንኳ ፤ ስለበዓሉ የሚያደርጉት አከባበርና ዝግጅት እንደየሀገሩ ባህሉም የተለያየ ነው ።

# በኢትዮጵያ የሚደረገው ዝግጅት

የትንሣኤ በዓል ከመድረሱ አስቀድሞ ከጾሙ አጋማሽ ጀምሮ ወንዱ ሠ ጋውን ሲቀልብ ፤ ፍየሉን ፤ በጉን ሲሞክት በጠቅላላው ለርድ የሚሆነው ፍሪዳ ሁሉ ሲያዘጋጅ ይሰነብታል ። ሴቶችም በበኩላቸው ቅቤውን ሲያንጥ በርበሬውን ሲደልሁ ፤ ለእንጀራ የሚሆነውን ዱቄት ሲያሰናዱ ፤ ለጠላ የሚ ሆነውንም እህል እየፈጩ ሲያጠራቅሙ ይቆያሉ ። በተጨማሪም አይቡ በልዩ ልዩ ቅመም መጣጣ ሲያደርጉና ባዶ (ወገሚት) የተባለውን በሺንክ ርት ፤ በጤና አዳም ጣዕሙ እንዳይለወጥ ሲቀምሙ ይሰነብታሉ ። በዓሉ ሲቃ ረብ ፤ የማንኛውም ነገር ዝግጅት ይከናወናል ። ለበዓሉ ዋዜማ የቅዳም ሥዑ ዕለት ማታ ከጸሎተ ሐሙስ ጀምረው ሲያከፍሉ የሰነበቱት ምእመናን ሁሉ ቦታ ቦታቸውን ይዘው የጊዜውን መድረስ ይጠባበቃሉ ። ከምሽቱ ፬ ሰዓ ሲሆን የክርስቶስን መነሣት የሚያበሥሩት የቤተ ክርስቲያን ደወሎች በየሰ ካቸው ድምፃቸውን ይሰጣሉ ። በዚህ ጊዜ በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ የተሰበ ቡት ሥነ ሥርዓቱን ለማክበር ይዘጋጃሉ ። ያልመጡትም ወደቤተ ክርስቲያ ጉዞአቸውን ይቀጥላሉ ። ከሴቶች ወገን ግን ሌሊት የሚገደፍበትን (የሚፈስክ በትን) መሰናዶ ስለሚያዘጋጁ ፤ ከአሮጊቶችና ከጥቂት ሴቶች በቀር ፤ በብዛ የጸሎቱና የቅዳሴው ተካፋይ አይሆኑም ። ቀጥሎም ከላይ እንደተናገርነው ዲ ቆኑ «ወተንሥአ እግዚአብሔር ከመ ዘንቃህ እምንዋም ፤» የሚለውን ምስባ በሰበከ ጊዜ ፤ ዙሪያውን የተሰበሰበው ሴቱም ፡ ወንዱም በጭብጨባና በልልታ ደስታውን እየገለጸና በኅብረትም ተሰጥዎ እየተቀበለ ይዘምራል ።

ከዚያም ቤተ ክርስቲያን ያዘጋጀችውን ጧፍ ለተሰበሰበው ሕዝብ ይታ ላል ። ያንን እያበሩ ካህናቱ እየዘመሩ ዑደት ሲያደርጉ ፤ ሕዝቡም አብረው በልልታ ሦስት ጊዜ ይዞራሉ ። በመጨረሻም ቅዳሴ ይቀደስና ቅዱስ ቍርባ ይሰጣል ። ከዚያም በኋላ ከዚህ ላደረሰው አምላክ ምስጋና እያቀረበ ለመፈሰ ወደቤቱ ይመለሳል ።

# በየጠቅላይ ግዛቱ ያለው የአፈሳሰክ ሥነ ሥርዓት

በሸዋ እንደ መረሐ ቤቴና መንዝ ይፋትና ቡልጋ ባሉት አውራጃዎች ሰ በቅቤ ይሠራና ግፍልፍል ሁኖ ይፈሰካል ። ለወላጅም ለዘመድም ለንስሐ አ ትም ለአክፋይ የሚወስደው ሥጋ ወጥ ተሠርቶ ግፍልፍል ሁኖ ነው ። አን



ንድ ጊዜ ደግሞ እንደተገኘ ሁለትም አንድም ቁና ዱቄት ለወላጅ ለንስሐ አባት ለአክፋይ ይወሰዳል ፤ በሌሎችም አውራጃዎች ቢሆን አክፋዮች የሆኑ የተ ልባ ጭልቃ ከጠጡ በኋላ ሁሉም በዕርጎ በአይብ በግፍልፍል ይገድፋሉ ። ለአክፋይ ግን የሚሰጠው እንጀራና ጠላ ነው ። ከትንሣኤው ጀምሮ እስከ ዳግም ትንሣኤ ድረስ እንኳን ጾመ ልጓሙን ፈታልህ እያለ ያረደውን በግ አብሮ በመብላት ጠላውንም አብሮ በመጠጣት በመጫወት ይሰነብታል ። በአዲስ አበባም ሆነ በሌሎች ከተማዎች የሚኖረው ሕዝብ ግን ድሮ ከቤት በተዘጋ ጀው እንጀራና ወጥ በተጠመቀውም ጠላ የመጠያየቁን ባህል ሠርዞ የውጭ ባህል በመከተል ጠላውን ወደውስኪ ወደኮኛክ ወደ ነጭ አረቄ እንጀራውን ወደ በግ ለውጦ የአክፋይ መውሰድ ጀምሮአል ።

በጐጃም ጠቅላይ ግዛት ደግሞ በዳሞትም ሆነ በአገው ምድር በተልባ በመጣጣ አይብና በወተት እንዲሁም እንጀራው ተደራርቦ ቅቤ ይቀባና ለመ ጀመሪያ ጊዜ በዚህ ይገደፋል ። ሲነጋ ግን ከብት ለሌላቸው ድኆች ሲዘጋጅ ከባጀው መጣጣ አይብና ወገሚት እንዲሁም ወተት ዕርጎ በልዩ ልዩ ዕቃ ልጆች እየወሰዱ እንዲሰጡ ይደረጋል ። ከዚህ በኋላ በግ ይታረዳል አብሮ መብ ላት እንጂ ልጅ ለወላጆቹ ዘመድ ለዘመዱ የአክፋይ መውሰድ የለም ለንስሐ አባትም ቢሰጥ ለደብረ ዘይት ነው ። በዚህ አኳኋን በጐጃም የሚገኙት አው ራጃዎች ከዚህ ጥቂት ቢለያዩ እንጂ ምንም ያህል ልዩነት የላቸውም ። በቤጌ ምድር ጠ/ ግዛት ደግሞ በስሜንና በወገራ እንዲሁም በአፈረዋናትና በእስቴ የተልባና የኑግ ፣ የሱፍ ጭልቃ ከማር ጋር ታሽቶ አክፋዮች በመጀመርያ ጊዜ ይህን ይጠጡና ከዚያ በኋላ በርጎ በአይብ በወተት በቅቤና በድልህ በተቀባ እንጀራ ይገድፋሉ ፤ ሲነጋ ዶሮ ያለው ዶሮ በግ ያለው በግ ያርዳል ። ይህንኑ ስምንት ቀን ሙሉ ሕዝቡ እየተጠራራ ከአንዱ ቤት ምሣ ከሌላው ቤት ራት እ… ሲበላና ሲጠጣ ይሰነብታል ።

በፋርጣና በጋይንት ያለው ይዞታ ከዚህ የተለየ ባይሆንም በአንዳንድ ቀበሌ የትንሣኤ ሌሊት የሰንበቴው ማኅበር አለቃ ወይም ሙሴ በግ ያርድና ጠብሶ ቀቅሎ ለማኅበረተኛው ሁሉ ያገድፋል ። ሥጋው ግን ሁሉም እንዲያ ልቅ ይደረጋል እንጂ አይተርፍም ፤ ወደቤትም አይወሰድም ስሙንም «ሠርክ በግዕ» ይሉታል ።

… እሥራኤል ያርዱት ከነበረው ከፋሲካው በግ ጋር ይመሳሰላል ፤ አንዳንዶቹም ይህንኑ ለዳግም ትንሣኤ የሚያደርጉ አሉ ። በዚህም ጠ/ ግዛት የቆየው ባህል አብሮ ከመብላትና ከመጠጣት በቀር ለወላጅም ሆነ ለዘመድ

የአክፋይ አይወሰድም ፤ ሌሎቹም አውራጃዎች በጥቂት ነገር ቢለያዩ እንጂ በብዙ ነገር አይለያዩም ፤ ይመሳሰላሉ ።

በትንሣኤ በዓል አከባበር በየጠቅላይ ግዛቱ በኩል ያለው ባህል የተለያየ አይደለም ፤ የሁሉንም ጠ/ግዛት በትንሣኤ በዓል ሰሞን ያለውን የሕዝብ ባህል ማቅረብ እንደሚገባን እናውቃለን ፤ ነገር ግን ልዩነቱ እስከዚህ የተራራቀ ባለመሆኑ አንድ በአንድ አልዘረዘርነውም ፤ የግብረ ሰላም እያሉ ቄጠማ ያዞሩትን ካህናት እየጠሩ ደግሞ ግብረ ሰላም ማብላት ግን በአብዛኛው ጠቅላይ ግዛት ፤ ያለው ሕዝብ ከጥንት የመጣ ባህል በመሆኑ ይተባበርበታል ።

## የትንሣኤ በዓል አከባበር በምሥራቅ ቤተ ክርስቲያን

የነሱም ትንሣኤ ከኛ ትንሣኤ ጋር አንድ ቀን ስለሚውል የአከባበሩን ሥነ ሥርዓት በሚከተለው ሁኔታ እናሳያለን ።

በግሪክ ሥርዓት ፤ በራሽ በጠቅላላው በምሥራቅ ቤተ ክርስቲያን የትንሣኤ ዋዜማ ክርስቲያኖች በታ በታቸውን አስቀድመው ይይዛሉ ፤ ሌሊት የሚበራውን መብራት ሕዝቡ ያመጣል እንጂ እንደ ኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያና አዘጋጅታ አታድልም ፤ የቤተ ክርስቲያኑ መቀመጫ ከመጥበቡ የተነሣ ካህናቱ አስቀድሞ ደጅ ለጠናው ምእመን የመቀመጫ ትኬት በነፃ ያድላሉ ይባላል ። ለምስጋና የተቀጠሩ ሆሮች ወይም ዘማሪዎች ግራና ቀኝ እየተቀባበሉ ይዘምሩታል ሕዝቡም አብሮ ይዘምራል ፤ በጾም ወራት በቤተ ክርስቲያኑ የነበረው ጥቁር ልብስ ሁሉ ይለወጥና ካህናቱ በሙሉ ነጭ ልብሰ ተክህኖ ለብሰው በመቅደስ ይቆማሉ ፤ በመጀመሪያ ክርስቶስ ተነሣ ብሎ የሚያውጀው ሊቀ ጳጳሱ ነው ፤ በዚህም ጊዜ ብርሃኑን ውሰድ እያለ በሕዝቡ እጅ ያለውን ጧፍ የሚያበራ ብርሃኑን የሚያካፍል እሱ ነው ፤ ሲያውጅም በአራቱ ማዕዘን ሦስት ሦስት ጊዜ ፊቱን እያዞረ ነው ፤ ብዙ ጳጳሳት ቢኖሩ በተራ ሁሉም እየተቀባበሉ ያውጃሉ ድንግሉም ቆሞሱም ሕጋዊውም ቢሆን አንደኛነት ያለው ካህን ያውጃል ፤ ቀጥሎም ክርስቶስ ተነሣ እየተባለ ሁደት ይደረጋል ፤ ወንጌልም በአራት ማዕዘን ይነበባል ። ቅዳሴ ከተቀደሰና ሕዝቡም ከቈረበ በኋላ ቤተ ክርስቲያን ቀያም ብላ ጥሩ የሥዕል ልምድ ያለው ሰው አስመጥታ ዕንቍላሉም እንዳይበላሽ ፡ሳክመዋለች ፤ ሠእሊውም በተቀቀለው ዕንቍላል ላይ ልዩ ልዩ ቀለም ያለው ሥዕል ይሠራበታል ። በላዩ ላይ የሚሳለውም የመስቀል የአክሊለ ሦክ ልዩ ልዩ



አስደሳች የሆነ ሐረግና አበባ በልዩ ልዩ ቀለም ይሳልበታል ፤ ይህም ለሊቀ ጳጳሱ ይቀርባል ፤ ሊቀ ጳጳሱም ክርስቶስ ከሙታን ተነሣ እያለ አንዳንድ ዕንቍላል ለሕዝቡ ሁሉ ያድላል ፤ ሕዝቡም በእውነት ተነሣ እያሉ የጳጳሱን እጅ እየሳሙ ይቀበላሉ ፤ ወደየቤታቸውም ከሔዱ በኋላ ከላይ የተጠቀሰውን ዕንቍላል ለዘመድ ለወዳጅ የስጦታ ልውውጥ ያደርጋሉ ዕንቍላሉንም እያጋጩ ሰላምታ ይሰጣጣሉ ። ክርስቶስም ከሙታን ተነሣ የሚለውን ሰላምታ እስከ ሃምሳ ቀን ድረስ በተገናኙ ቍጥር እንደ ሰላምታ ይለዋወጣሉ ፤ ምሳሌውም ከተደፈነ ዕንቍላል ውስጥ ሕይወት ያለው ዶሮ እንደሚወጣ ሁሉ ክርስቶስም ከተዘጋ መቃብር መነሣቱን ያመለክታል ይላሉ ።

## ማ ጠ ቃ ለ ያ

ስለትንሣኤ በዓል አከባበርና የሚደረገውንም ባህል በመጠኑ ከተረዳን ይህንኑ የትንሣኤን በዓል ምክንያት በማድረግ በአዲስ አበባም ሆነ በየጠቅላይ ግዛቱ ያለው ዝግጅት በቀላሉ የሚገመት አይደለም ብዙ ገንዘብ ወጭ ተደርጎ ለበዓሉ አከባበር አስፈላጊ የሆነው የቤት ውስጥ መሰናዶ ሁሉ እንደ አስፈላጊነቱ እየተገዛ ይቀርባል ። በዓሉም በየዓመቱ ተደጋግሞ ስለሚመጣ በርከት ያሉት ቤተሰቦች በዚህ በትንሣኤ በዓል አማካይነት ተከታዩን ቀን በመዘንጋት ለአንድ ቀን ደስታ ሲሉ የወሩን ባጀት በማቃወስ ከአቅማቸው በላይ በርከት ያለ ገንዘብ ወጭ ያደርጋሉ ።

ከዚህም የተነሣ በትንሣኤ በዓል ጊዜ የሚወጣውም ገንዘብ ከፍተኛ በመሆኑ በየአንዳንዱ ቤተሰብ ላይ ከፍ ያለ ጉዳትን ስለሚያስከትል አቅም በፈቀደ መጠን ማዘጋጀት ብልህነት ነውና ቢታሰብበት መልካም ነው ።

ሆኖም እውነተኛ ክርስቲያን ላንድ ቀን ትንሣኤ ብቻ የሚሠራ ሳይሆን ፤ ለዘላለማዊ ሕይወቱ መደገፊያ የሚሆነውን ማውጣት ማውረድ እንዳለበት ለዚህም ቀን ሊያወጣ ተገቢ መሆኑን ጨርሶ መዘንጋት የለብንም ።

ወደመንፈሳዊው ዓላማ መለስ ያልን እንደሆን ደግሞ በጥንቱና በአሁኑ ትውልድ መካከል ብዙ ልዩነት እንዳለ እንረዳለን በጥንቱ ትውልድ ትንሣኤ የሚከበረው የቤተ ክርስቲያን ተካፋይ ሆኖ ነበር እንጂ እንዳሁኑ ጊዜ በልዩ ልዩ ጌጥ ማጌጥ ስጦታ በመለዋወጥ ፤ አብዝቶ በመብላትና በመጠጣት ፤ በመስከርም አልነበረም ።

የአሁኑ ግን ከልክ ባለፈ ግብገር በዳንስ ፤ በዕረፍት ፣ በምቾት ፤ በሽርሽር ይከበራል እንጂ ስለመንፈሳዊነትና በቤተ ክርስቲያን ተገኝቶ የማክበር ፍላጎትና ስሜት በጣም እየቀዘቀዘ በመሔድ ላይ ነው ። እንዲህ ያለው ይዞታ ያሰጋው ጁንማንስታርያን የተባለው ሊቅ «ለሰው ልጅ ከማንኛውም ነገር ሁሉ ዋና ፈንጠዝያው ቅዱስ ቍርባንን መጋበዝ ነው የመጀመርያውም የመጨረሻውም ደስታ ይህ ነበር ። ዛሬ ግን ማንኛውም ሰው ለተራው ግብገር ስላዳላ መንፈሳዊው ምንጭ በመድረቅ ላይ ነው» ሲል ተናግሮአል ።

እንዳለውም የሰው ልጅ ከመንፈሳዊ ደስታ ይልቅ ለሥጋዊው ደስታ እያዳላ በመሔዱ በጣም ያሳዝናል ። ከዘላለማዊውም ምግብ ይልቅ የኃላፊውን ምግብ ግብገር እያበለጠ በማሰቡ ዘላቂ ሕይወቱን የረሳ ይመስላል ። እንዲህ ያለው ሁኔታ ወደፊት ሥር እየሰደደ እንዳይሔድና ሁኔታውም እንዳይስፋፋ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከአሁኑ መፍትሔ ቢፈልጉለት መልካም ነው ።

አለቃ ነቢየ ልዑል የሐንስ ።

# የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን

# በተቀዳሚ ማድረግ የሚገባት

በአሁኑ ክፍለ ዘመን በቤተ ክርስቲያናችን ላይ የሚሰማው ትችትና የሚሠነዘረው የነቀፌታ ድምፅ እጅግ በጣም እየበረከተ መሔዱን ሁላችንም እናውቃለን ። በክርስቶስ የተመሠረተችው ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን በመልካምና በቀና መንገድ ተራምዳ ከግቧ ለመድረስና የሌሎች ክፍለ ዓለማት አብያተ ክርስቲያናት ከደረሱበት ግብ ለመድረስ እንድትችል ሰፊ የሆነ የትምህርት ፕሮግራምና የሠለጠኑ ሠራተኞች ያስፈልጓታል ።

ቤተ ክርስቲያናችን ከጥንት ጀምራ የሥልጣኔ መሪ እንጂ ተመሪ አይደለችም ። የዕውቀት በር ፣ የሥልጣኔ ምንጭ መሆኗ በሁሉም ዘንድ የተመሰከረላት ናት ።

የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን ለተለዩ ሰዎች መጠቀሚያ የተመሠረተች ድርጅት አይደለችም ፤ የተመሠረተችው በጠቅላላ የክርስቶስ ቤተ ሰብ ለሆኑ ሁሉ ሲሆን ፤ ዓላማዋም በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ደም የተገኘውን አዲስ ሕይወት ፤ የኃጢአትን መንፃት ፤ የዲያብሎስን ድል መነሣት ማስተማርና በክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ የተገኘውን ድል ላልሰሙት ወገኖች ማብሠር ነው ።

የቤተ ክርስቲያን መሠረት የሆነው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለአገልግሎት የመረጣቸውን ደቀ መዛሙርት አስተምሮ በሚገባ ካሠለጠነ በኋላ ዓለሙን በጠቅላላ ዞረው እንዲያስተምሩ ሲልካቸው የሰጣቸው መሪ ትእዛዝ «ሒዱና ወንጌልን ለዓለም ሁሉ አስተምሩ» የሚል ነበር ። ደቀ መዛሙርቱም የትምህርት አሰጣጥ ዘዴና ልዩ ጸጋ ስለነበራቸው በሕዝብ ዘንድ መወደድ ፤ በእግዚአብሔር ዘንድ ባለሟልነት ነበራቸውና የቤተ ክርስቲያንን መሠረት ለማጽናት በቅተዋል ።

ዛሬ ያለንበት ክፍለ ዘመን ሥጋዊውን ትምህርት ተሳታፊዎች የበረከቱበት ፤ የቤተ ክርስቲያንን ትምህርት ፈላጊዎች በጣም ያነሱበት መስሎ ይታያል ። ስለዚህም በዚህ ክፍለ ጊዜ ቤተ ክርስቲያናችን ከመቸውም ይልቅ በየ

በልጥ ነቅታ ፤ ተግታ ትምህርቷ ተቀባይነት እንዲኖረው መሥራትና የማስተማር ተግባሯን ልታከናውን የሚገባት መሆኑን ማወቅና መረዳት ይኖርባታል።

ከመነሻው እንደተጠቀሰው ቤተ ክርስቲያናችን በቅድሚያ ልትፈጽመው የሚገባት ምንድር ነው ? በሚለው ቃለ ጥያቄ ከብዙ ሊቃውንት ፤ ሽማግሌዎችና ወጣቶች ጋር ብዙ ውይይት አድርገን ነበር ። የሁሉም አስተሳሰብ በአንዳንድ ነገር የተለያየ መስሎ ቢታይም ፤ ዓላማው ያው ተመሳሳይ ነው ። እንደሁሉም አስተያየት ቤተ ክርስቲያናችን ከሁሉ አስቀድማ ልታደርገው የሚገባት የትምህርት ይዞታዋን ማሻሻልና ማስፋፋት ሆኖ ተገኝቷል ።

# ት ም ህ ር ት

ቤተ ክርስቲያናችን ከሁሉ ተግባሯ አስቀድማ በየጠቅላይ ግዛቱ ፤ በየአውራጃው ፤ በየወረዳውና በየቀበሌው ትምህርት ቤቶች በብዛት እንዲከፈቱ ማድረግ ተገቢዋ ነው ። በነዚያ በምትከፍታቸው ትምህርት ቤቶችም በመጽሐፍ ቅዱስ ፤ በቅዳሴና በመሳሰሉትም መንፈሳውያን ትምህርቶች ብቻ ሳትወሰን የሕክምና ፤ የእርሻ ፤ የተግባረ እድ ፤ የአስተዳደር ፤ የቋንቋ ፤ የማኅበራዊ ኑሮና የመሳሰሉትም የትምህርት ዓይነቶች ተቀላቅለው እንዲሰጡ ማድረግ ተገቢ መሆኑን በመግለጽ የሁሉም ድምፅ ያስተጋባል ። ምክንያቱም ዘመኑ የዕድገት ፤ የልማት ጊዜ በመሆኑ ፤ ቤተ ክርስቲያን ከዚህ ተለይታ የሥራ ፈት አብነት መስላ እንዳትገመት ነው ። በትጋት ካስተማረች ቤተ ክርስቲያናችን የሚደርስባትን ችግር ሁሉ ተቋቁማ ድል በመንሣት የሌሎች ክፍለ ዓለማት አብያተ ክርስቲያናት ከደረሱበት ለመድረስ የሚያዳግታት ነገር አይኖርም ።

ከቤተ ክርስቲያናችን ክልል ወጣ ብለን ስንመለከት የቀለም ፤ የተግባረ እድ ፤ የጦር ፤ የሕክምና ፤ የንግድ ፤ የእርሻ ፤ የሕግና የመሳሰሉትም ትምህርት ቤቶች በብዛት ተከፍተው ሥራቸውን በሚገባ ጊዜውን ተከትለው ሲያከናውኑ እናያለን ። ይሁን እንጂ ፤ በመንፈሳዊ በኩል ያላቸው ዝንባሌ የተሟላ ባለመሆኑ ፤ በተሰለፉበት የሥራ መስክ አልፎ አልፎ የሞራል ውድቀት ይታይባቸዋል ። ይህንን የመሰለውን ጉድለት ለማሟላት የቤተ ክርስቲያናችን ኃላፊነት ስለሚጠይቅ ፤ ቤተ ክርስቲያናችን የትምህርት ፕሮግራሟን በሚገባ አዘጋጅታ በያንዳንዱ ክፍለ ትምህርት እየገቡ ለማስተማር የሚችሉ መምህራንን ማሰለፍ ይኖርበታል ።



የቆየውን የትምህርት ይዞታ ሳይለቁ ፤ ዘመናዊውንም ትምህርት ሳይንቁ ሁለቱንም በአንድነት ቀምመውና አጣጥመው ፤ ለሕዝብ ተስማሚ አድርገው የሚያቀርቡ ሊቃውንት ከተገኙ የቤተ ክርስቲያናችን እርምጃ የቀና እንደሚሆን አይጠረጠርም ። ሕዝቡም እንደ ዝናመ ምሕረት ቀና ብሎ አንጋጦ አሁን አሁን ይወርድልናል ብሎ የሚመለከተው ይህንን ነው ።

# አ ስ ተ ዳ ደ ር

በአሁኑ ጊዜ ቤተ ክርስቲያን ካሉባት ችግሮች አንዱ የሚገባውን ለሚገባው ከማድረጉ ላይ ነው ። ለምሳሌ ወታደሩን ቀድስ ፤ ገበሬውን ነግድ ፤ ነጋዴውን እረስ ፤ ሌላውንም የሚያውቀውን ሥራ አስትቶ በማያውቀው የሥራ መስክ ቢያሠማሩት ፤ የሥራውን አቋም ሆን ብሎ ማሰናከል ይሆናል ። ሁሉም በሚያውቀው ሥራ ከተሰለፈ ግን የሥራው እርምጃ የተቃና ከመሆኑም ሌላ ፤ አሠሪውንም ሆነ ሠራተኛውን እጅግ ያስመሰግናል ። ስለዚህ የተጀመረው ሥራ ሁሉ መልካም ውጤት እንዲኖረው ከተፈለገ ፤ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ኃላፊነት ያላቸው ምሁራን ፤ በብሉይና በሐዲስ ኪዳን ትምህርት ብቻ የተወሰኑ ሳይሆኑ በአስተዳደርና በዘመናዊ ትምህርት የበለጸጉ ሁነው መገኘት አለባቸው ። እንደዚህ ከሆነ ቤተ ክርስቲያናችን በጥሩ ሁኔታ ወደፊት ለመራመድ ትችላለች ። በርግጥ ቤተ ክርስቲያናችን ለዘመናዊው ሥልጣኔ ተካፋይነቷ ባይቀርም ፤ የተፈለገባትን ያህል አሟልታ ትራመዳለች ብሎ ለመናገር እያስደፍርም ። ብዙ የሚቀሯት ነገሮች አሉ ። በተለይ በአስተዳደር በኩል ያለው እርምጃ በጣም አስደሳች መስሎ አይታይም ።

እንዲያስተዳድሩ ከሚሾሙት ሊቃውንት አብዛኞቹ ኃላፊነታቸውን የዘነጉ ፤ የማስተማር አቅድ የሌላቸው ናቸው ። አንዳንዶቹ ደግሞ ዕውቀታቸው በዳዊትና በተሰጥዎ ብቻ የተወሰነ ነው እየተባለ ይተቻል ። «ከእነርሱም አለመሠልጠንና አለመማር የተነሣ ፤ በቤተ ክርስቲያን ሰዎች ዘንድ የሥራ መንፈስ እንዳይኖር ሆኗል»ሲል አንድ የቤተ ክርስቲያን ሰው አስተያየቱን ሰንዝሯል ።

በቤተ ክርስቲያናችን የተማሩም ቢገኙ ፤ በየችሎታቸው የሚያሠማራቸው ባለመኖሩ ፤ ሁልጊዜ በተመሪነት ቦታ በመገኘታቸው ወቀሳው አብሮ ሲያገኛቸው ፤ ራሳቸውንም ሆነ ቤተ ክርስቲያናቸውን ሳያሻሽሉ ይኖራሉ ። እንዲያውም የቤተ ክርስቲያናችን አቋም እንደመንግሥታችን አቋም ሲሆን

ሥልጣን አክፋፍሎ የማሠራቱ ዘዴ ባለመገለጹ ለሁልጊዜ ምሥጢር ሁኖ ይኖራል ።

ያለፈው አለፈ ለወደፊቱ ግን የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ለመሆን የሚፈለጉ ሊቃውንት በዕውቀት የበሰሉ ፤ በአስተሳሰባቸው ፤ በትምህርታቸው የተራቀቁ ፤ የሥራ ጊዜያቸውን አገባደው ለጡረታ ደረጃ ያልደረሱ ፤ ወጣትነት ያላቸው ፤ ለሕዝቡ እንደራሳቸው አድርገው የሚያስቡ ፤ በጠባይም በኩል ጉድለት የሌለባቸው ፤ ፈሊጠኞች ፤ የዘመኑ ሁኔታ በደንብ የገባቸው ቢሆኑ የቤተ ክርስቲያናችን ሥራ የተቃና እንደሚሆን የሁላችንም እምነት ነው ።

## አ ገ ል ግ ሎ ት

በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ ተሰልፈው በሚገባ አገልግሎታቸውን እንዲያበረክቱ የሚጠየቁ የተለዩ ሰዎች አይደሉም ። ቤተ ክርስቲያን የሁሉም ናትና ። ሁሉም ወገኖች አገልግሎታቸውን እንዲያበረክቱ ይጠየቃሉ ። ቀሳውስቱና ዲያቆናቱ በቅዳሴ ፤ መዘምራኑ በማኅሌትና በቅኔ አገልግሎታቸውን ሲያቀርቡ ምእመናኑ ደግሞ ከወጡበት ፤ ከወረዱበት ገንዘባቸው አስተዋጽኦ በማውጣጣት ስለ ቤተ ክርስቲያናቸው ዕድገት ጠንክረው መሥራት ይኖርባቸዋል ።

በቀድሞ ጊዜ በየቤተ ክርስቲያኑ የክርስቲያኖችን አኗኗርና ዕድገት የቤተ ክርስቲያንንም አገልግሎት በቅርብ ሁነው መመልከት ያለባቸውና ሥነ ሥርዓቱም በሚገባ እንዲካሔድ የሚያደርጉ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ነበሩ ። በኋላ ግን እየዋለና እያደረ ወደ ጳጳሳት ፤ ወደ ቀሳውስትና ዲያቆናት ተላለፈ እየተባለ ይነገራል ። ሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ዛሬ በዓለም ላይ እንሠራርተው የሚገኙት ሊቃውንቱና ሕዝበ ክርስቲያኑ ፤ ወንድ ፤ ሴት ፤ ትንሽ ፤ ትልቅ ሳይሉ በመተባበር የሚገባቸውን ግዴታ እየንዳንዳቸው በማወቃቸው ነው ። የእኛም ቤተ ክርስቲያን አባሎች የሚፈለግባቸውን አገልግሎት በሚገባ ከፈጸሙ ቤተ ክርስቲያናችን የሌሎች ክፍለ ዓለማት አብያተ ክርስቲያናት ከደረሱበት ግብ ለመድረስ የሚያዳግታት የለም ። በተጨማሪም የካህናቶቻችን አገልግሎት ሰዓት ሳይወስኑ ተግቶ ነቅቶ በማስተማር እንጂ ሌሊት ሰዓታት ቁሞ በማደርና በመቀደስ ብቻ መወሰን የለበትም ። ይህንን ያልተረዱና ያላወቁ አንዳንድ በስም ካህናት ነን ባዮች መንደር ለመንደር መዞርንና ወሬ ማውራትን እንደ ዕለት ሲሳይ አድርገው ይኖራሉ ። ከሁሉም የሚያሳዝነው ጉባኤ



አስፍተው ምሥጢር አብራርተው አንዳንድ ሊቃውንት በሚናገሩበት ጊዜ ፤ ልዩ ልዩ ስም በመስጠት እነርሱ ብቻ እውነተኞች መስለው ሕዝቡ እንዳይቀበል መከልከላቸው ነው ። እንዲህ ያለው ዘመን ፈሪሳውያን አልፎ በስም ብቻ ሳይሆን የግብር ካህናት የሚነሡበትን ጊዜ እንናፍቃለን ።

## ሹ መ ት

ቤተ ክርስቲያናችን ለወጣቶችና ለሽማግሌዎች መልካም አርአያ ማሳያ ስለሆነች ፤ መመሪት ያለባት በተማሩ ባወቁና በጠነቀቁ ሹማምንት ሊሆን ይገባል ። ከዚህም ጋር ኢትዮጵያዊነታቸውን እንጂ ጐሣቸውን ባለመመልከት ፤ ሞያቸውን እንጂ ወገናቸውን ባለማየት የቤተ ክርስቲያኑ አባሎች የሆኑትን ሁሉ ማሠማራት ይኖርባቸዋል ። ለምሳሌ ስንዴ ለመሥዋዕት ተስማሚ የሆነው ስንዴ በመሆኑ እንጂ ቀላ ወይንም ደጋ በመብቀሉ አይደለም (አይመረጥም)እንደዚህ ከሆነ ምእመናኑም ሆኑ ካህናቱ የቤተ ክርስቲያን ፍቅር ስለሚያድርባቸው ስለእርሷ ደኅንነትና ዕድገት ጠንክረው ከመሥራት ወደኋላ አይሉም ።

የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ፤ ካህናትና ምእመናን ተባብረው በአንድነት ከሠሩ ፤ ቤተ ክርስቲያናችን መንፈሳዊ እርምጃዋን አስተካክላ ለመራመድ ትችላለች ። በሥልጣኔ ከገፉት አብያተ ክርስቲያናትም ጋር ጐን ለጐን ለመሔድ አይሳናትም ።

አንዳንድ ሰዎች ቤተ ክርስቲያናችን በቅድሚያ መፈለግ ያለባት የገንዘብ ምንጭ የሚገኝበትን መንገድ ነው ። ገንዘብ ካገኘች በትምህርት ሊቃውንቱን እያሠለጠነች ፤ ሹመት ለሚገባው ሹመትን ፤ ማስተማር ለሚገባው ማስተማርን ፤ ሌላውም በየችሎታው እንዲሠማራ ለማድረግ ትችላለች ይላሉ ። ሌሎች ደግሞ በተቃራኒ መንገድ ይናገራሉ ። ምክንያቱም ገንዘብን የሚፈጥረው ሰው በመሆኑ ፤ ከገንዘብ በፊት ዐዋቂና ሠራተኛ መገኘት ያስፈልጋል ። እንደተባለው ቤተ ክርስቲያንን ለጊዜው ያጠቃት የገንዘብ ችግር ሳይሆን ፤በአንድ በኩል የጥንቱን ትምህርትና ባህል ከአዲሱ ጋር አዋሕደው ለሕዝብ ጆሮ ተስማሚ አድርገው የሚያቀርቡ ሊቃውንት ማጣት ነው ። በሁለተኛው በኩል ደግሞ የነበራትን ሀብት ሁሉ ሰብስቦ በደንበኛው መዝገብ መዝግቦ ይዞ በተገቢው [illegible]ውል ብልህ ሠራተኛ ባለመገኘቱ ነው ።

በተጨማሪም ቤተ ክርስቲያናችን ከምእመናኑ ጋር የምትዛመድበትን መንገድ አብራርተው የሚያስተምሩ ምሁራን ከተገኙ ፤ ቤተ ክርስቲያናችንን የገን

ዘብ ችግር ሊያጠቃት አይችልም ። የገንዘብም ምንጮቿ ፤ ባጀቶቿ ምእመናን ናቸውና ። ይህንንና ይህንን የመሰለውን ማዘጋጀት ያለባቸው ደግሞ የቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪዎች ናቸው ።

## ስ ብ ከ ት ።

ስብከት የቤተ ክርስቲያን አንዱ ታላቁ የአገልግሎት ክፍል ነው ። ከአ ሁን ቀደም የነበሩት የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት በጊዜው ለጊዜው ተፈላጊ ሆኖ የተገኘውን ስብከት ለምእመናን በማበርከት ተደናቂነትን እያገኙ አልፈ ዋል ። በዚያን ጊዜ ዘመኑ በሚፈቅደው መንገድ ስለአስተማሩ በሕዝቡ ዘንድ ተደንቀዋል እንጂ አልተነቀፉበትም ።

ዘመን ወደኋላ ይቀራል እንጂ ወደፊት ቀድሞ አይገኝም ። ዛሬ ያለፈው ዕለት ነገ ተመልሶ አይመጣም ። ነገ ደግሞ የሚያልፈው ፤ ከዚያ ወዲያ የሚ ከተለው ፤ ዕለት እንደፈሳሽ ውኃ ነውና የሚገሠግሠው ወደፊት ስለሆነ ፤ ሊገታ አይችልም ። የጊዜው ትውልድ እንደጥንቱ አቴናውያን ጠባይ ያለ ጠባይ ስላለው ፤ ሁልጊዜ አዲስ ነገርን ለመስማትና ለማየት ይጓጓል ። ነገሩ የሚከፋ ባይሆንም ፤ «ባለው ላይ ቁሞ አዲስ ነገርን ለማግኘት የሚጣጣር ሰው ሁልጊዜ ወደፊት ይሔዳል» የሚባለውን አነጋገር ማስታወስ ያስፈልጋል ።

«ስብከት ከሰው ጥረቶች አንደኛው ክፍል ነው » እንደሚባለው ፤ የሞ ራል ስብራት ያገኘውን ለመጠገን ፤ የተዛባውን አሳምሮ አቃንቶ በትክክል እንዲራመድ ለማድረግ ስብከት ፍቱን መድኃኒት ሁኖ ተገኝቷል ።

በስብከት ዘዴ የሠለጠኑ ምሁራን ካሉ ፤ ወጣቶቹም ሆኑ ሽማግሌዎች ፤ ሴቶችም ሆኑ ወንዶች ፤ ከቤተ ክርስቲያን ትምህርትና ሥነ ሥርዓት የሚርቁ በት ምክንያት ሊኖር አይችልም ። የቤተ ክርስቲያናችን የትምህርቷ ፤ የሥር ዓቷና የችግሯ ሁሉ ተካፋዮች ይሆናሉ ።

ክርስቶስ ሲያስተምር የአምስት ገበያ ሰው የሚያህል ሕዝብ ይከተለው ነበር የሚባለው ፤ ከስብከቱ አስደሳችነት የተነሣ ነው ። በስብከቱ ተማርከው ሕዝቡ እህል መብላትን የዘነጉበት ጊዜም እንደነበረ ይነገራል ። እንዲሁም ከጊታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ቀጥለው ሐዋርያት ሲያስተምሩ ፤ ስብከታቸው እጅግ በጣም ተወዳጅነት ስለነበረው ፤ በትምህርታቸው አሰጣጥ የተደሰቱት ምእመናን ልብሳቸውን ፤ ምግባቸውን እያውጡ ይረዷቸው ነበር ።



ዛሬም ቢሆን እውነተኞች ሰባክያን ከተገኙ ፤ በምእመናን ዘንድ ከፍ ያለ ተወዳጅነት ሊኖራቸው እንደሚችል አያጠራጥርም ። ዛሬ በቤተ ክርስቲያናችን ላይ የወደቀባት ትልቅ ችግር መስሎ የሚታየው ፤ እንደ ሐዋርያት በስብከት ዘዴ የሠለጠኑ ምሁራን በብዛት አለመገኘታቸው ነው ። « ሰማይ ተነዶ ይጫ ንህ ፤ መሬት ተከፍቶ ይዋጥህ ፤ ይሰበርህ ፤ ይሰንጥርህ ፤ መዓት ያውርድብህ



ሰባኪዎቻችን እነዚህ . . . . . ናቸው ።

ያሉ ምእመናንን የሚያባብሩና የሚያሸብሩ ፤ የሚዘልፉ አንዳንድ በትምህርት ያልተሞረዱ ሰባኪዎች የሚሰጡት ስብከት ቤተ ክርስቲያናችንን ሊያስጠላት ስለሚችል ፤ እነርሱ ተወግደው ለዘመናዊው ትውልድ ተገቢውን ትምህርት የሚያበረክቱ ሰባክያን ቢሰለፉ የቤተ ክርስቲያን ሥራ የተቃና ሊሆን ይችላል ተብሎ ይታመናል ።

እንደ አውሮፓ ዘመን አቈጣጠር በ፲፱፻፵፯ ዓ. ም. ማስተማር የጀ
ውን አሜሪካዊ ዶክተር ልጠቅስ እፈልጋለሁ ። ይህ ዶክተር የስብከት
ጣጥ ዘዴ ስለነበረው ፤ በስብከቱ ተስበው ክርስቶስን ለመቀበል የወሰ
ሰዎች ቍጥር ወደ አንድ ሚሊዮን ተጠግቶ ነበር ይባላል ። ዶክተሩ ዓለ
እየዞረ በሚያስተምርበት አደባባይ ፤ በየዕለቱ የሚጐርፉት አድማጮች ከ
ሰባው ከኻያ አምስት ዓመታት ዕድሜ በታች የሆኑት ወጣቶች እንደሆኑ
ገራል ። ዶክተሩ ወጣቱን የሚስበው በጣዕመ ስብከቱ ነው እንጂ ፤ ሌላ
ዘዴ የለውም ። አንድ አስተዋይ ሰው «አብያተ ክርስቲያናት ኀላፊነታቸ
በመርሳትና የሠለጠኑ ሰባክያንን ባለመመደባቸው ውድቅ የሆኑ ድርጅ
ለመሆን የተቃረቡ መሆናቸውን ያለፈ ታሪክ ይመሰክርባቸዋል ። ስለዚህ
ብያተ ክርስቲያናት ላይ የሚሰሙት ነቀፌታዎች ትክክል መሆናቸው የ
ካድ ነው » ሲል ከሰባክያን ጉድለት የተነሣ በአብያተ ክርስቲያናት ላይ የ
ደርሰውን ጉድለት ገልጾ ተናግሯል ።

በርግጥ ሰባክያን በሚገባ ከሠለጠኑ ፤ ለሕዝብ የሚስማማውን ትምህ
አበጥረው ስለሚያውቁት ለአዲሱ ትውልድ የሚስማማውን የትምህርት
ነት መስጠት አያዳግታቸውም ። «በሕዝብ ፊት ቆመህ የምታስተምረው ት
ህርት ፤ ሰውን የሚጠቅም እንዲሆን እንጂ ፤ የአንተን ዐዋቂነት ብቻ የ
ልጽ አይሁን» የሚል የአበው አነጋገር አለ ። የሥልጣኔ አየር የነፈሰባቸ
ሰባክያን የሚሰጡት ትምህርት ፤ በሁሉም ዘንድ ተወዳጅነት አለው ። የ
ክርስቲያናችንም ሰባክያን እውነቱን ከሐሰት ግልጽ አድርገው ካስተማሩ ፤
ክርስቲያናችን በሐዲስ ትንሣኤ እንዳትነሣ እጇዋን ይዞ የሚያስቀራት የለ

አሁን ባለንበት ክፍለ ዘመን የሚገኘው ትውልድ ፤ በየዕለቱ አዲስ
ይን ፤ አዲስ ምድርን እየሁ እያለ የሚያፈችል ስለሆነ ፤ የሚቀርብለት ት
ርት በአዲስ መንገድ የተዘጋጀ እንዲሆን አጥብቆ ይፈልጋል ። ታላቁ ሐዋ
ጳውሎስ ከኢየሩሳሌም ወደ ደማስቆ በሚያመራው ጐዳና ላይ እንዳለ ፤ በ
ረቅ ወላፈን ዓይኑ ጠፍቶ አዲስ የብርሃን ጮላጮልን ካገኘ በኋላ ፤ የሮ
ግዛት ዳር እስከ ዳር እየተዘዋወረ የክርስትናን ስብከት ለብዙ ሕዝብ አዳር
ሁሉም አዲስ ስለሆነለት እነሆ ማንኛውም አለፈ ፤ ሁሉም አዲስ ሆነ ፤ የ
ቁርና ዘመን ፈጽሞ ጠፋ ። ከእንቅልፍ የመነሻው ጊዜ ደረሰ ፤ ሌሊቱ ኦለ
ቀንም መጣ ሲል የስብከቱን ውጤት በአጭር አነጋገር አጠቃሎ ተና
ነበር ። የቤተ ክርስቲያናችንም ሊቃውንት የክርስቶስን ቃል እንደ ሐዋር
እንደ ቅዱስ ጳውሎስ ለምእመናን ነቅተውና ተግተው ማብሠር አለባቸው ።



የሌሊት ወፎች ዓይኖቻቸው የቀን ብርሃንን አተኩረው ለመመልከት እንደማይችሉ ሁሉ ፤ በክርስትና ትምህርት የለሰለሰ ልብ የሌላቸው ሰዎችም ከቤተ ክርስቲያን አጠገብ ሲደርሱ ዓይነ ልቡናቸው ስለሚታወር ፤ የሚሔዱበት ጐዳና ደብዝው ጠፍቷቸው ከጉዳት ላይ ይወድቃሉ ። ይህንና ይህን የመሰለው ጥፋት በምእመናን ላይ እንዳይደርስ ለቤተ ክርስቲያናችን የቆየውን ከሐዲሱ ጋር አዛምደው ፤ አገናዝበውና አስማምተው የሚያስተምሩ ሰባክያን በብዛት ያስፈልጓታል ። ቤተ ክርስቲያን ከሁሉም አስቀድማ ማስፋፋት የሚገባት የትምህርት ይዞታዋን መሆኑ በሁሉም ዘንድ ታምኖበታልና ።

ከቈስ ልሳነ ወርቅ በዛብህ

# የአብያተ ክርስቲያናት አንድነት

« ሰዎች የእግዚአብሔር ልጆች እንዲሆኑ እግዚአብሔር የሰው ልጅ ሆነ » ይላሉ ፤ ቅዱስ አትናቴዎስና ሊቁ ዮሐንስ አፈወርቅ የእግዚአብሔርንና የሰው ተዋሕዶ በተረጐሙበት ክፍል ። ታላቁ ነቢይ ኢሳይያስም ሰው የሆነው አምላክ «አማኑኤል» ይለዋል ፤ እግዚአብሔር ከኛ ጋር ማለት ነው ።

እንግዲህ የክርስትና ምሥጢር ድንቅነት ፤ የክርስቲያኖች አንድነት ፤ የተ መሠረተው ከዚህ ላይ ነው ። በዚህች የክርስቲያኖች አንድነት ሰዎች ሁሉ በማስተዋል ፤ በትዕግሥት ፤ በእውነተኛ ፍቅር ፤ በርኅራኄ ፤ በብርታት ፤ አር በማስተዋል ፤ በትክክለኛነት ፤ በገርነት ፤ በልበ ሰላም ፤ ራሳቸውን ገዝተው የ ለዓለም ሕይወትን እንዲወርሱ ቃል ሥጋ ሆነ ። ለተቀበሉት ሁሉ በስሙ ለሚ ያምኑት የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው ። እነርሱም ከእግዚአብሔር ተወለዱ ። እኛ ሁላችን ከምልአቱ ተቀብለን በጸጋ ላይ ጸጋ ተ ጥቶናልና ። ዮሐንስ ፩ ፤ ፲፪-፲፯

ጸጋ በጸጋ ላይ የሚገኝባት ቤተ ክርስቲያን ከተመሠረተች እነሆ ፲፱፻፷ ዓ. ም. ሆኗታል ። የበጎ ነገር ሁሉ እናት በመሆኗ የደረሰባት መከራ ከ መኑ ቀናት የበለጠ ነው ። በልጆቿ መካከል የተደጋገመ አለመግባባት ግጭት ደም መፋሰስ ደርሷል ። የተጣሉትን ልጆቿንም ለማስታረቅ ብዙ የእርቅ ሸንጎ ዎች ተደርገዋል ። መልካም ውጤትን ያሳዩት ግን አንደኛ የኒቅያ ጉባኤ (፫፻፳፭ ዓ. ም. ሁለተኛው ቍስጥንጥንያ (፫፻፹፩) ዓ. ም. ሦስተኛው የኤፌሶን (፬፻፴፩ ዓ. ም. እነዚህ ጉባኤዎች ናቸው ። በነዚህ ጉባኤዎች አማካይነት ቤተ ክርስቲያ እንዲ ፤ ቅድስት ፤ የሁሉ በላይ ፤ የሐዋርያት ጉባኤ ፤ የተባሉትን ግብሯን አመሠራረቷን የሚገልጡትን ቅጥሎች ተቀዳጅታለች ። በጸሎተ ሃይማኖ [illegible] ዘወትር ስትወሳ ትኖራለች ።

ይሁንና ይች አንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በአምስተኛው መቶ ዘመ በ፬፻፶፩ ዓ. ም. በጉባኤ ኬልቄዶን ላይ በደረሰባት ሃይማኖት ለበስ የሥልጣ ሽሚያ ጦርነት ከምን ጊዜም የከፋ ዕድል ገጥሟት ከሁለት ተከፈለች ። ል ቿዋም አውጣኪአውያንና ንስጥሮሳውያን መባባል ጀመሩ ። « ጠላት ይቀባ ጥላት » እንደተባለው ሁሉ አንዱ ክፍል ሌላውን ጥላት መቅባት ጀመረ ። ብ ተካረረ ። እርስ በርስ መወጋገዝ እግዚአብሔርን እንደማገልገል ተቆጠረ ።

በ፩፻፶፬ ዓ. ም. ደግሞ ለብዙ ጊዜ በክብረ ነክ ጉዳይ ሲቃቃሩ የቆዩ የሮምና የባይዛንታይን አርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ተወጋግዘው ተለያዩ



በ፩ሺ፭፻፲፯ ዓ. ም. ማርቲን ሉተር ፤ ዘጠና አምስት አንቀጽ ያዘለውን መቃወሚያ ጽሑፉን በዊተንበርግ ቤተ ክርስቲያን በር ላይ የቸነከረበት መዶሻ የካቶሊክን ቤተ ክርስቲያን ከሁለት ከፈላት ። ከዚያ በኋላማ ስማቸውንና ቍጥራቸውን እንኳ ለማጥናት እስኪያዳግት ድረስ የቤተ ክርስቲያን ዘርፎች በዙና ልዩ ልዩ የእምነት ሥርዓቶች ተነዙ ።

እነሆ ያች አንዲ ሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን በዚህ ዓይነት ሁኔታ መገኘቷ ለስሟ መጥፋት ፤ ለተቃራኒዎቿ ምቾት ፤ መሆኑን የተገነዘቡ የኬልቄዶንና የቀዳምያን ኬልቄዶን አርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ሊቃውንት የክርስቲያኖች አንድነት የሚፈጠርበትን ፤ የቤተ ክርስቲያን ስም የሚታደስበትን መንገድ በመሻት በዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር « የእምነትና ሥርዓት » ክፍል አማካይነት ልዩ ውይይት ሲያደርጉ አሁን አራተኛ ጊዜያቸው ነው ።

<u>የመጀመሪያው ልዩ ውይይት</u> በአርሁስ ዩኒቨርስቲ ዴንማርክ እ/ ኤ/ አ/ ከነሐሴ ፲፩—፲፭/፲፱፻፷፬ ዓ. ም. ከላይ የጠቀስናቸው እትማማች አብያተ ክርስቲያናት ፲፭ ሊቃውንት ከሽህ አምስት መቶ ዓመታት በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ፊት ለፊት ቀርበው ስለ ሃይማኖት ተወያዩ ።

ቤተ ክርስቲያን ከሁለት እንድትከፈል ምክንያት የሆናት የኬልቄዶን ጉባኤ ፬፻፶፩ ዓ. ም. ስለነበረ ፤ ያንን ጉባኤ አንሥተው ፤ «ሰው የሆነው ቃለ እግዚአብሔር አንድ ባሕርይ ፤ « አሐዱ ባሕርይ ዘእግዚአብሔር ቃል ሥግው » ስለሚለው የቅዱስ ቄርሎስ የእምነት መግለጫ ኃይለ ቃል ቀደም ብለው በየበኩላቸው [illegible]ዮቻቸው የጥናት ጽሑፎች ላይ በወንድማማችነት መንፈስ ተነጋገሩ ፤ ተከራከሩ ፤ ያልተብራራውን አብራሩ ። በመጨረሻም አለያይቷቸው የኖረ የፖሊቲካ ጉዳይ እንጂ የአንድ ባሕርይና የሁለት ባሕርይ ይትበሃል አለመሆኑን ተረዱ ። « እኛ በአንድ አካል አንድ ባሕርይ በፍጹም ተዋሕዶ » ስንል ፤ እነሱም «በአንድ አካል ሁለት ባሕርያት በተዋሕዶ በሚሉበት ጊዜ ሁለቱም ወገኖች ያለመከፈል ፤ ያለመነጣጠል ፤ ያለመጠፋፋት ፤ ያለመለወጥ ፤ የባሕርየ ሥጋንና የባሕርየ መለኮትን ፍጹም ተዋሕዶና መገናዘብ ስለሚያምኑ ፤ ልዩነቱ የቃላት አገላለጥ እንጂ የእምነት አለመሆኑን በጋራ መግለጫቸው በአንድ ቃል አጸደቁ ።


ሁለተኛው ልዩ ውይይት በብሪስቶል ዩኒቨርሲቲ ኢንግላንድ (እ. ኤ. አ.)
በ፲፱፻፷፯ ተደረገ ። ይኸ ውይይት የአርሁስን ስብሰባ ውጤት የተከተለ
ሲሆን ጠቅላላ መንፈሱ ከዚያ የተለየ አልነበረም ። ሊቃውንቱ የኬልቄዶ
ንን ጉባኤ ፬፻፶፩ ዓ. ም. ምክንያት አድርገው ፤ የኤፌሶንን ጉባኤ (፬፻፴፩) ተመ
ርኩዘው «ስለጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም ሰውነት»ከሊቃውንቱ በቀረቡት
ጥናቶች መሠረት ሐሳብ ለሐሳብ ተለዋውጠው ሁለቱም ወገኖች በልዩ ልዩ
ቃላት አንድ ዓይነት የእምነት ትምህርት ሲያስተምሩ መኖራቸውን አረጋግ
ጠዋል ። አሥር አንቀጾች የያዘ የጋራ መግለጫም አውጥተዋል ። ጌታችን ኢየ
ሱስ ክርስቶስ ፍጹም ሰው ፍጹም አምላክ መሆኑን በአንድ ቃል መስክረው ፤
ያለፈውን የአርሁስን የጋራ መግለጫ እንደገና አጽድቀዋል ።

ሦስተኛው ልዩ ውይይት ደግሞ እንደ ኤ/ አ/ ከነሐሴ ፲፯—፳፩ /፲፱፻፸
ዓ. ም. (በሴናክል) ጀኔቫ ተደርጓል ። በአለፈው የተደረጉት ጉባኤዎች ስምም
ነትም በድጋሚ ጸድቋል ።

በጀኔቫው ውይይት ሊቃውንቱ በልዩ ልዩ አርእስት ያዘጋጁዋቸውን ጽሑ
ፎች ተመርኩዘው «ትክክለኛው እምነት ስለተገለጠባቸው ኃይለ ቃላትና ስለ
ሥርዓተ ቀኖና» ተነጋግረዋል ። ያሳለፉትም የጋራ መግለጫ የመጀመሪያ
ረቂቅ ቍ ፬ እንደሚነበበው ፥ ስምምነታቸው ከትምህርተ ሥጋዌ አልፎ
የቀዋሚውን ባህልና ሥርዓት ሙሉ ሐሳብ እንደሚያቅፍና በሚያስፈል
ገው ሁሉ ማለት በማኅሌትና ውዳሴ ቅዳሴ ፤ በእምነትና በሥርዓተ ቀኖና ፤
ስለቅድስት ሥላሴ ፤ ስለ ሥጋዌ ስለመንፈስ ቅዱስ አካልና ሥራ ፤ ስለመሠ
ረተ ቤተ ክርስቲያን በአገልግሎትና በምሥጢራት የቅዱሳን አንድነትና
ጌታ በክብር ሲመጣ ዓለም ስለሚኖረው ሕይወት ፤ ባደረጉት ጥናት ሁለቱ
ቤተ ሰብ አብያተ ክርስቲያናት የአንዲት ቤተ ክርስቲያን የጋራ ቀዋሚ ቅዱስ
ባህልና ሥርዓት ሲያስተምሩና ሲጠብቁ እንደኖሩ ለማወቅ በቅተዋል ። ይሁን
እንጂ ምንም እንኳ በመሠረታዊው ጉዳይ ቢስማሙም የብዙ ዘመን ሳይቀራረቡ
መኖር በአገልግሎቱና በአፈጻጸሙ በኩል መጠነኛ ልዩነት መኖሩን ባለመ[ገ]
ጋት ተጨማሪ ጥልቅ ጥናት እንዲደረግ ተስማምተዋል ። በጠቅላላም ስለተነ
ጋገሩበት ዝርዝር ጉዳይ ፲፪ አንቀጾችን የያዘ የጋራ መግለጫ ረቂቅ አሳልፈ
ዋል ።



አራተኛው ልዩ ውይይት የተደረገው እንደ ኤ. አ. ጥር ፳፱—፳፫ ፤ ፲፱፻፸፩
ዓ. ም. አዲስ አበባ ውስጥ በግዮን ሆቴል የመሰብሰቢያ አዳራሽ ነው ። የዓ
ለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር ማዕከላዊ ኮሚቴ ስብሰባ እንደ ተፈጸመ ፤
ይኸ ልዩ ውይይት እንዲደረግ ቀደም ብሎ ታስቦ ስለነበር «ውግዘት ይነሣ ፤
የቅ... ክብር ይወሳ» በሚል ርእስ ተነጋግረዋል ። ለውይይቱ ሰፊ ሐሳብ
እንዲሰጡ ከሁለቱም ወገን የቀረቡት ጽሑፎች ተነበው ክርክር ተደርጎባቸ
ዋል ። እንዳለፉት ውይይቶች ሁሉ የዚህም ስብሰባ መሠረተ ሐሳብ ከኬልቄዶን
ጉባኤ የራቀ አልነበረም ። ምክንያቱም ሁለቱ ወገኖች ተወጋግዘው የተለያ
ዩት በዚህ ጉባኤ ስለነበረ ውግዘቱ እንዴት እንደ መጣ መርምረዋል ።
ኬልቄ...ውያን ልዮንን ጻድቅ ፥ ቅዱስ ዲዮስቆሮስን መናፍቅ ሲሉ ፤ የኬልቄ
ዶን ...ቃዋሚዎች ደግሞ ልዮንን መናፍቅ ዲዮስቆሮስን ጻድቅ እንላለን ። ምክ
ንያቱ ሲመረመር ግን ቅዱስ ዲዮስቆሮስ በኛ ዘንድ ሥነ ሥርዓትን ጠብቆ
እምነቱን አጽድቆ የተገኘ ቅዱስ ነው ። በነሱም ዘንድ ቢሆን የጉባኤ ሥነ ሥርዓት
(ዲስፕሊን) አንደልክ ተብሎ እንጂ ከቅዱስ ቂርሎስ ትምህርት ነጥብ እንዳልጨ
መረና እንዳልቀነሰ ራሳቸው ኬልቄዶናውያን በዚሁ ስብሰባ አረጋግጠዋል ። ንሶ
ጥሮስና ...ለውጣኬ በሁለቱም እኅትማማች አብያተ ክርስቲያናት መወገዛቸው በድ
ጋሚ ተረጋግጧል ። በዚህም ምክንያት ለአብያተ ክርስቲያናቱ አንድነት አመሠ
ራረት የእምነቱ አንድነት ቀዳሚነትን እንደያዘ «ቂም ይዞ ጸሎት ሳል ይዞ ስር
ቆት» የለም እንደሚባለው ሁሉ ፤ በአምስተኛው መቶ ዘመን የነበረው ፖለ
ቲካን ...ት ቤተ ክርስቲያንን የከፋፈላት አለመግባባት ከጊዜው ጋር ይለፍና
አሁን ... ባንዱ የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ መግባት ስለማይችል ፤ እነ ቅዱስ
ዲዮስቆሮስ ፤ እነቅዱስ ሳዊሮስና ልዮንን በመሳሰሉት ላይ የተላለፈው ከእም
ነት ውጪ የሆነ ውግዘት ይነሣ ፤ የቅዱሳኑ ስም በየአብያተ ክርስቲያናችን
እንደገና ይወሳ ፤ በማለት በወንድማማችነት መንፈስ ሰፊ የሐሳብ መለዋ
ወጥ ተደረገ ። ምንም እንኳን ፩ሺ፭፻ ዓመታት ሙሉ የተጻፉትን መጻሕፍት
ለማረ... ...እመናኑንም አእምሮ በቀላል ለመለወጥ አዳጋች መሆኑ ቢታወቅም
ቢያንስ ቢያንስ ውግዘቱ ከእንግዲህ ወዲህ በይፋ እንዳይነበብ ተስማምተው ፤
፲፪ አንቀጾችን የያዘ የጋራ ስምምነት አጽድቀው ፤ በፍጹም የመግባባት መን
ፈስ ተሰነባብተዋል ። መጽሐፉም ለመታተም በመዘጋጀት ላይ ይገኛል ።



፬ኛው ውይይት ይህን የመሰለ ነበር (አዲስ አበባ)

በዚህ ውይይት ከሌሎቹ ውይይቶች ይልቅ በርከት ያሉ ኢትዮጵያው
ያንና ሌሎቹም የኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ወኪሎች ሊቃውንት ተ
ኝተዋል ። ይህም ጉባኤውን ይበልጥ እንደረዳውና ሞገስ እንደሰጠው የው
ይቱ ሊቃነ መናብርት ከልብ ገልጠዋል ።

በውነቱ በዚህ አጋጣሚ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር ሊመ
ገን ይገባዋል ። እነዚህ አራት ልዩ ውይይቶች እንዲደረጉ የረዳና ለመልካ
ውጤትም ያበቃቸው በውስጡ የሚገኘው ፌይዝ አንድ ኦርደር «የእምነት
ሥርዓት ክፍል » ሲሆን የዚሁ ክፍል ኃላፊ ዶክተር ሉቃስ ፊሸር ብዙ ረ
ተዋል ። የእነዚህ ውይይቶች ውሳኔዎችና የቃለ ጉባኤው ፍሬ ሐሳቦች በል
ልዩ ጥራዝ ታትመው ስለወጡ ፤ አብዛኞቹ አብያተ ክርስቲያናት አንብበው ተ
ድተዋል ። አስተያየታቸውንም በሊቃውንቶቻቸው አማካይነት ገልጠዋል
በኛ በኩል እስካሁን የወጣ መግለጫ ባለመኖሩ ምእመናንም ሆነ ምሁራን የ
ይይቶቹን ፍሬ ነገር በመጠኑ እንዲረዱት ይህን አጠቃላይ መግለጫ በቀላ
ለመጻፍ ሞክረናል »



ምንም እንኳ ጉባኤዎቹ የምሥራቅና የመካከለኛው ምሥራቅ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ሊቃውንት ልዩ ውይይት « በመባል ቢታወቁም ፡ ያቀረባቸው ጥናቶችና ያሳለፉቸው ውሳኔዎች በጣም ጠቃሚዎች መሆናቸውን የሁለቱም ወገን አብያተ ክርስቲያናትና ሊቃውንት ስለተረዱት በቅርቡ በነዚህ እኅትማማች አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች ወይም በሙሉ ሥልጣን የሚወክሏቸው ሊቃውንት ምልአተ ጉባኤ ቀዋሚ ( ኦፊሴል) የጋራ መግለጫ አውጥቶ ለአያሌ ዘመን በልዩ ልዩ ምክንያት ተለያይተው የኖሩት ቤተ ሰቦች አንድ እንደሚሆኑ ይታመናል ። በዘመናችን እንደሚፈጸምም የሁላችን ክርስቲያናዊ ተስፋ ነው ።

አንድ ጸሎተ ሃይማኖት አለን ። ባሕርየ መለኮትና ባሕርየ ሥጋ ያለመከፈል ፤ ያለመነጣጠል ፤ ያለመጠፋፋት ፤ ያለመጉደል መጨመር ፤ በፍጹም ተዋሕዶ በመገናዘብ ፤ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም አምላክና ፍጹም ሰው መሆኑን ሁላችንም እናምናለን ። ቤተ ክርስቲያንን አንዲት ፤ ቅድስት የሁሉ በላይ ፤ የሐዋርያት ጉባኤ ፤ የሚያሰኛት ይኸ ስለሆነ አንድ የማንሆንበት ምክንያት አይኖርም ።

ከአበባው ይግዛው

# የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር አመሠራረትና ዓላማው

ስለ ቤተ ክርስቲያን እውነተኛ ትንቢት ሲተነበይለትና ዘመን ሲቈጠርለት
ከቆየ በኋላ ለመጀመሪያው ሰው ለአዳም የተሰጠው የድኅነት ተስፋ በተፈጸመ
ጊዜ ዓለምን ለማዳን ከክብር መለኮታዊ ዙፋኑ የወረደው መድኀኔ ዓለም ክር
ስቶስ ወደዚህ ዓለም በአካለ ሥጋ መጥቶ በመስቀል ላይ ባፈሰሰው ቅዱስ
ደሙ ዋጅቶ ከኃጢአት ተገዢነትና ከዲያብሎስ ባርነት ያላንዳች ዋጋ ፈጽሞ
ነፃ ካወጣን በኋላ እኛን በስሙ ክርስቶሳውያን ወይም ክርስቲያን ፤ እርሱን ለማ
መስገንና ለማምለክ ባንድነት የምንሰበሰብባትን ቦታ ደግሞ ቤተ ክርስቲያን
ብሎ የሰየመው መድኃኒታችን የመንፈሳዊ ሥራው መጀመሪያ ያደረገው ፤
ቅዱስ ዓላማውን ባንድ መንገድ የሚከተሉለት ፲፪ ሐዋርያትንና ፸፪ አርድ
ዕትን ፤ እንዲሁም ፴፮ ቅዱሳት አንስትን በመምረጥ እርሱ አለቃዋ ወይም
እናቷ የሆነላት ቤተ ክርስቲያንን መመሥረት ሲሆን ፤ ከዚያ ዘመን በኋላ ግን
በየጊዜው የተነሡት የሱና የሐዋርያት ተከታዮች የነበሩ የቤተ ክርስቲያን መሪ
ዎች ከግል ጥቅምና ክብር ፈላጊነት የተነሣ በመካከላቸው ብዙ አለመግባባ
ትንና የመለያየት እክልን እየፈጠሩ መሔድ ስለተጀመረ ፤ አንዳንድ ከበድ
ያለና አከራካሪ የሆነ የሃይማኖት ጉዳይ በገጠመ ቍጥር ታላላቅ በዘመናዊው
አጠራር ዓለም አቀፍ ጉባኤዎችን እያደረጉ ከተወያዩ በኋላ የተግባቡባቸው
ጊዜያቶች ቢኖሩም ቅሉ የቤተ ክርስቲያንን አንድነት ያፈረሱባቸው ጉባኤዎ
ችም ቍጥር ያነሰ ሁኖ አልተገኘም ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ያወቀቻቸውና በታ
ሪክ መዝገብ የሠፈሩት ሦስቱ ዓበይት ጉባኤዎች ሲሆኑ ፤ በተለይ ከኬልቄዶን
ጉባኤ ፬፻፶፩ ዓ ም ወዲህ በአብያተ ክርስቲያናት መሪዎች መካከል ብዙ አለ
መግባባትና መለያየት አጥብቆ እየጠነከረ ሄዶና ባንድ ክርስቶስ መሥራችነት
ተመሥርታ አሐቲ እየተባለች ስትጠራ የነበረች ቤተ ክርስቲያን ከፍ ብሎ
እንደተጠቀሰው ሁሉ በመሪዎቿ የግል ጥቅምና ከንቱ ክብር ፈላጊነት ምክንያት
በየጊዜው በብዙ ዓይነት ቍጥር እየተከፋፈለች ብዙዎች የሆኑ ሰው ሠራሽ
ስሞችን አበጀች ።

መሥራቿ ክርስቶስ እንኳን ወደዚህ ዓለም የመጣበትን ሥራ ሁሉ ፈጽሞ
ወደሰማይ ለማረግ በተነሣበት ወቅት የጸለየው የመጨረሻ ጸሎት «አባት ሆይ



እኔና አንተ አንድ እንደሆንን የሰው ልጆች ሁሉ አንድ ይሆኑ ዘንድ ፈቃድህ
ይሁን የሚል ነበር (የዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ ፲፯ ቍጥር ፳፩)

ዳሩ ግን ይህ ሁሉ ሆኖ ሳለ የሰው ልጆች የዚህን አምላካዊ ጸሎት ንባብ
እንጂ ትክክለኛ ትርጉም ልብ ብለው ባለመገንዘብ እነሆ በሆነ ባልሆነው
ምክንያት ባንድነት ፈንታ መለያየትን እያስፋፉና እርስ በርሳቸው እየተወጋ
ገዙ መሔድን ቀጠሉ ።

በዚህም ሁኔታ ቀደም ሲል ኦርቶዶክስና ካቶሊክ በሚል ስም ከሁለት
ተከፍላ የነበረችውን ቤተ ክርስቲያን በ፲፮ኛው ክፍለ ዘመን ማርቲን ሉተር
የተባለው ጀርመናዊ መነኰሴ ከሮማ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን አባልነቱ ባን
ዳን[illegible] የሃይማኖት ነክ ጉዳዮች አለመግባባት ምክንያት ተለይቶ ከሄደበትና
ሌላ ፕሮቴስታንት የተባለ ሃይማኖትን ከፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ የቤተ ክርስቲ
ያን መከፋፈል ይዞታ እየተስፋፋ መሔድን ቀጠለና ቤተ ክርስቲያንን ከአስጊ
ሁኔታ ላይ እንድትወድቅ ሊያደርጋት ቻለ ። ማርቲን ሉተርም በመንፈሳዊ
ዓለም አካባቢ በየጊዜው ቍጥራቸው የበዛ ተከታዮችን በፈጣን ሁኔታ እያገኘ
መሔድን ጀመረ ። በኋላም እርሱን የመሰሉ ሌሎች ሰዎች ( እነጆን ካልቪን ) በየ
በከ[illegible]ው ካንዲት ቤተ ክርስቲያን እየተገነጠሉ የራሳቸውን ሃይማኖት በመ
ፍጠር ሌሎች አብያተ ክርስቲያናትን ማቋቋም ጀመሩ ።

ስለዚህም እነሆ በዚህ ዓይነት የመለያየት ይዞታ ነገሩ ሁሉ ከጊዜ ወደ ጊዜ
መልኩን እየለወጠና ያለመግባባቱ ሁኔታ እየቀጠለ ከመባባስ ደረጃ ላይ ደረ
ሰና አንደኛው ሌላውን በመንቀፍ እንዲሁም በክርስቶስ መሥራችነት ተመ
ሥር[illegible] አንዲት የነበረች የክርስትና ሃይማኖትን እንደየስሜታቸው በመተርጐም
ስለ[illegible]ፈሏት አሁን በያዝነው ኻያኛ ክፍለ ዘመን በምትታይበት አቋም ቤተክር
ስቲያን የብዙዎች ዓይነቶች እምነቶች መጠሪያ ስም ሁና ትገኛለች ፤ አንዲት
ቤተ ክርስቲያንም በማለት ፋንታ አብያተ ክርስቲያናት ይባላሉ ።

ከብዙዎች ዘመናት በኋላ ግን በተለይ በዚህ በኻያኛ ክፍለ ዘመን የተነሡ
የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ይህ መለያየት የተባለው ነገር በኋላ ዘመን በሰው
ልጆች (በዘመኑ በነበሩ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች) የግል ጥቅምንና ከንቱ
ው[illegible] በመፈለግ ምክንያት የተፈጠረ ሰው ሠራሽ ነገር እንጂ ከመሥራቹ
ክርስቶስ ያልተገኘ አጉል የጥፋት ይዞታ መሆኑን በመገንዘብ ፤ ተሰርዞና ተበ
ላሽቶ የነበረውን የአንድነት ዓላማ እንደገና ለመመሥረት ብዙ ጥናት ካደረጉ
በኋላ የስሙ ልዩነትና ብዛት አይጥፋ እንጂ በመነቃቀፍ ፈንታ መግባባት በመ
ራራት ፈንታ መቀራረብ ፤ በመለያየት ፈንታ አንድነትን መፍጠር አስፈላጊ

መሆኑ ስለተደረሰበት ፤ እውነተኛውን የአንድነት ዓላማ ለመመሥረት ከሁሉ አስቀድሞ በጉባኤ መልክ እየተገባበዙ መንፈሳዊ ውይይትን ማድረግ ማስፈለጉ ታመነበት ።

ስለዚህም ዋናው የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር ከመቋቋሙ በፊት ከዚህ እንደሚከተለው በተራ ቊጥር የተዘረዘሩት ልዩ ልዩ ጉባኤዎች ተደርገዋል ።

እነሱም ፤

፩ኛ/ በ፲፱፻፪ ዓ. ም. ኤዲንብራህ በተባለው የእስኮትላንድ ዋና ከተማ ላይ ፡ የዓለም የወንጌል መልእክተኞች ጉባኤ «እምነትና ሥነ ሥርዓት » በሚል ርእስ ስብሰባ ተደረገ ።

፪ኛ/ በ፲፱፻፲፫ ዓ. ም. በዚሁ በኤዲንብራህ ከተማ የወንጌል መልእክተኞች ምክር ቤት ዓለም አቀፍ ጉባኤ «ሕይወትና ሥራ» በሚል ርእስ ስብሰባ ተደረገ ።

፫ኛ/ በ፲፱፻፲፯ ዓ. ም. በስዊድን ዋና ከተማ በእስቶክሆልም ሌላ ዐቢይ ስብሰባ ተደረገ ።

፬ኛ/ በ፲፱፻፲፱ ዓ. ም. ከስዊዝ ዋና ከተማ ከጄኔቫ በስተሰሜን በኩል ከምትገኝ ለሚዛኔ ከተባለች የባሕር ዳርቻ ከተማ ላይ ሌላ ታላቅ ጉባኤ ተደረገ ።

፭ኛ/ በ፲፱፻፳ ዓ. ም. በኢየሩሳሌም ተደረገ ።

፮ኛ/ በ፲፱፻፳፱ ዓ. ም. በኤዲንብራህና ለንደን ከተማ ውስጥ በሚገኘው በኦክስፎርድ በተከታታይ ጉባኤዎች ተደረጉ ።

፯ኛ/ በ፲፱፻፴ ዓ. ም. በኔዘርላንድስ ማዕከላዊ ግዛት በኡትሬችና በሕንድ ሀገር በሚገኘው በማድራስ ከተማ ሌሎች ሁለት ጉባኤ ተደረጉ ።

፰ኛ/ በ፲፱፻፴፱ ዓ. ም. በእንግሊዝ ሰሜናዊ ክፍል ግዛት በምትገኝ ሁይትቢ በተባለች የባሕር ዳርቻ ከተማ ላይ ሌላ ተመሳሳይ ጉባኤ ተደረገ ።

፱ነኛ/ በ፲፱፻፵ ዓ. ም. በሆላንድ ዋና ከተማ በአምስተርዳም ላይ ታላቁ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር የመጀመሪያው ታሪካዊ የመመሥረቻ ጉባኤ አደረገ ። በዚህም ዐቢይ ጉባኤ የልደት በዓል ላይ ከ፩፻፵፯ አባል አብያተ ክርስቲያናት የተላኩ ፫፻፶፩ መንፈሳውያን መልእክተኞች የተገኙ ሲሆን የጉባኤውም ርእሰ ነገር «አብሮ መኖር» የሚል ነበር ።

፲ኛ/ ከዚህም ታሪካዊ የክርስቲያኖች አንድነት ጉባኤ በኋላ የማኅበሩ ሕይወት ሰጪና የደም ሥር የሆነው ማዕከላዊ ኮሚቴ በ፲፱፻፵፬ ዓ. ም. ከኒው ዚላንድ ዋና ከተማ በስተደቡብ ከባሕር ዳርቻ በምትገኘው በዊሊንግቶንና በስዊድን ዋና ከተማ በእስቶክሆልም ውስጥ በምትገኝ ሉንድ በተባለች ከተማ (ዩኒቨርስቲ) ላይ የመጀመሪያዎቹን ዓበይት ጉባኤዎች በተከታታይ አደረገ ።



፲፩ኛ/ ከዚያም ቀጥሎ በ፲፱፻፵፮ ዓ. ም. ሁለተኛውን የማኅበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ከአሜሪካ ጠቅላይ ግዛቶች አንዷ በሆነችው በቺካጎ የገጠር ከተማ በኢቫንስቶን ላይ ተደረገ ። በዚህም ታላቅ መንፈሳዊ ጉባኤ ላይ ከ፩፻፷፫ አባል አብያተ ክርስቲያናት የተላኩ ፮፻፪ መንፈሳውያን መልእክተኞች ተካፋዮች እንደ ነበሩ ለማወቅ ተችሏል ።

፲፪ኛ/ ማዕከላዊው ኮሚቴ ሦስተኛውን ጉባኤ በጋና ዋና ከተማ በአክራ በ፲፱፻፶ ዓ. ም. አደረገች ።

፲፫ኛ/ ሦስተኛው የማኅበሩ ጠቅላላ ጉባኤ በሕንድ ዋና ከተማ በኒውዴልሂ ተደረገ ። በሦስተኛው የማኅበሩ ጠቅላላ ጉባኤም ላይ ከ፩፻፺፩ አባል አብያተ ክርስቲያናት የተላኩ ፭፻፸፯ መልእክተኞች ተካፋዮች ነበሩ ሲል የማኅበሩ ጠቅላላ ጉባኤ መግለጫ ያስረዳል ።

፲፬ኛ/ ሌሎች መለስተኞች ጉባኤዎች በ፲፱፻፶፭ ዓ. ም. በሜክሲኮና በሞንትሪያል (ካናዳ) በተከታታይ ተደርገዋል ።

፲፭ኛ/ በ፲፱፻፶፰ ዓ. ም. የዚሁ ዓይነት መጠነኛ ጉባኤ የማኅበሩ ጠቅላይ ጽሕፈት ቤት በሚገኝበት በጄኔቫ ከተማ ላይ ተደርጓል ።

፲፮ኛ/ በ፲፱፻፷ ዓ. ም. የማኅበሩ አራተኛ ጠቅላላ ጉባኤ ከስዊድን ግዛት በስተምሥራቅ በኩል በምትገኘው በኡፕሳላ ከተማ ከፍ ባለ ድርጅት ተከናውኗል ።

በዚህም አራተኛ የማኅበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ላይ ከ፪፻፴፭ አባል አብያተ ክርስቲያናት የተላኩ ፩ሺ፫፻፪ መልእክተኞች ተካፋዮች መሆናቸው ታውቋል ። የጉባኤውም ርእስ ነገር « ሁሉን ነገር አዲስ አደርጋለሁ» የሚል ነበር ።

በእውነትም አተኩሮ ሲመለከቱት ባሁኑ ጊዜ ሁሉ ነገር አዲስ ነው ። የሰው ልጅ እጅግ ከተራቀቀ ዘመን ላይ ደርሷል ። ሬዲዮው ፤ ስልኩ ፤ ቴሌቪዥኑ የጠፈር መመርመሪያው መሣሪያ ሁሉ ዘመን የወለደው ጥበብ ሲሆን ፤ ለተመለከቱ ብርቅና ድንቅ የሆኑ ድርጊቶችን የሚያሳይ ነው ። በሌላ አንጻር ሲመለከቱት ደግሞ በሰው ልጅ እጅ የተፈለሰፉ ልዩ ልዩ የጦር መሣሪያዎች ያስከተሉት በዓለም ዙሪያ ያለው ጦርነትና ረኀብ ችግር ፤ በሌላው በኩል ደግሞ የቦታን መጥበብና የኑሮን ጠቅላላ ችግር እየባባሰው በመሔድ ላይ የሚገኘው የሕዝብ ቊጥር ብዛት ዓለምን ከፍ ካለ ሥጋት ላይ ጥሏታል ።

መግለጫው እንደሚያስረዳው ሁሉ አራተኛው የዓለም አብያተ ክርስቲያ
ናት ማኅበር ጠቅላላ ጉባኤ በኡፕሳላ በተሰበሰበበት አጭር ጊዜ ውስጥ ይህ
ሁሉ የዓለም ችግር ተደምሮ በዘመናችን በተለይ የክርስትና ሃይማኖት ስለ
ጠመው ዕንቅፋት ተወያይቶ መፍትሔ መስጠት በጣም አስቸጋሪ ቢሆንም ይህ
ጉባኤ ዓለምን ለገጠማት ከባድ ችግር መድኃኒት ለማስገኘት እያንዳንዱ ክር
ቲያን አዘውትሮ መጸለይ ያለበት መሆኑን አስገንዝቧል ። ክርስቶስ በመከራው
ወቅት ደቀ መዛሙርቱ ሐዋርያትን ከመኝታቸው እየቀሰቀሰ ነቅታችሁና ተ
ታችሁ ጸልዩ ሲል ማዘዙን ቅዱስ መጽሐፍ ይናገራል ። ዛሬ ሁላችንም እን
ምናየው ሁሉ ዓለም ብትወድቅ ዳግመኛ ለመነሣት ከቶ ከማትችልበት ገደል
አፋፍ ላይ ተንጠልጥላ ትገኛለች ። ስለዚህ እንዳትወድቅ ተረዳድቶ መደገ
በላይዋ የሚኖረው ሕዝብ ግዴታ ነው ። እያንዳንዱ ሰው (የሰውን ልጅ ሕ
ወት ማጥፊያ መሣሪያዎች የፈለሰፉት ሳይንቲስቶች ሳይቀሩ) በአእምሮው (ማ
ያስበው ፤ በእጁ የሚሠራው ነገር ሁሉ የሚጨብጥ ፍሬ ነገርን አሳጥቶት ፤ መ
ፈሱን የሚያሳርፍበት ፤ ስሜቱን በትክክል የሚገልጽበት መንገድ አጥቶ በአ
ላቅ ጭንቀት ላይ ይገኛል ። ስለዚህ ይህን ጭንቀት አስወግዶ የመንፈስ ዕረ
ትን ለማግኘት ክርስቶስ እንዳዘዘው ተግቶ መጸለይ ያስፈልጋል ።

ይህ ኻያኛ ክፍለ ዘመን አቴይዝምና ማቴሪያሊዝም የነገሡበት ዘመን ስ
ሆን ፤ የሰው ልጅ ሰውነቱን እንዳይዘነጋ እነሆ የዓለም አብያተ ክርስቲያና
ማኅበር ባንድ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ጉባኤ በሚያደርግበት ወቅት የመላው
ዓለም ሕዝበ ክርስቲያን ጸሎት ከተጨመረበት ዓለማችንን የገጠማትን ረቂ
ጠላት ድል መንሣት ብዙ አያዳግትም ።

፲፰ኛ/ በ፲፱፻፷፫ ዓ. ም. የማኅበሩ ማዕከላዊ ኮሚቴ አራተኛውን ዐቢ
ጉባኤ ጥንታዊት የክርስትና ደሴት ተብላ በምትጠራው ኢትዮጵያ ዋና ከተ
በአዲስ አበባ ላይ እጅግ በጣም በደመቀና አስደሳች በሆነ ይዞታ አከናው
ስለብዙዎቹ ጉዳዮች ውሳኔዎችን አሳልፏል ።

ይህ ዓለም አቀፍ የሆነ መንፈሳዊ ድርጅት (ማኅበር) ከዚህ በላይ በየተ
በተዘረዘሩት ዓመታትና ቦታዎች ባደረጋቸው ዐበይትና ንዑሳን ጉባኤዎች ል
ልዩ የሆኑ ከፍተኛ የሰብአዊ መብት ማስከበርና የእርስ በርስ መግባባት ግ
ላይ የሚያደርሱ ውሳኔዎችን ያስተላለፈ ከመሆኑም በላይ የተባበሩት መንግ
ታት ማኅበርን ቀዋሚ ዓላማ በመደገፍ ከዓለም አቀፍ ድርጅት ጋር በመተ
በር በተፈጥሯቸው የእኩልነት መብት ያላቸውን ወገኖች ሰብአዊ መብት የ
ክዱትንና በጭቆና አገዛዝ የሚገዙትን ጥቂቶች ሕገ ወጦች መንግሥታ



ማለት እንደቡብ አፍሪካንና እንፖርቱጋልን ፤ እንዲሁም ሕገ ወጡን የሮዴሺያ መንግሥት አውግዞ ለነፃነት ተዋጊዎችም የሞራልና የገንዘብ ርዳታውን አድርጓል ፤ እንዲሁም በያስፈላጊው ጊዜ ያደርጋል ።

ባሁኑ ጊዜ ማንኛውንም ዓይነት ሥራ ብቻን መሥራት እጅግ አዳጋች ነው ። ተባብሮ መሥራት ፤ ባንድነት እየተሰበሰቡ መወያየትና በማኅበር መጸለይም የክርስትና ሃይማኖት አዋጅ ነው ። አንዱ ክርስቲያን ለሌላው እንዲጸልይ ክርስቶስ በዚህ ዓለም በነበረበት ጊዜ አጥብቆ አስተምሯል ።

ይህ ከሆነ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበርም ቀዋሚ ዓላማ ከዚህ የተለየ አይደለም ። የውስጥ ደንቡን በዝርዝር ገባ ብሎ ማተት ባያስፈልግም እንኳ እያንዳንዱ በክርስቶስ እምነት የተመሠረተ ቤተ ክርስቲያን በመተባበር በመግባባትና በመረዳዳት ፤ እንዲሁም አንደኛው ለሌላው በመጸለይ ጭምር የክርስትናን ትምህርት በሕይወቱ ሥጋ ላሉ ምእመናን ሁሉ ያላንዳች አድልዎ ማስተማርና የክርስቶስ ቤተ ሰቦች ማድረግ ሕጋዊ ተግባር መሆኑን አለመዘንጋት ይገባል ።

የክርስቲያን ሕይወት የመናኝ ጉዞን ስለሚመስል ፤ እያንዳንዱ ክርስቲያን የሚኖረው የእግዚአብሔርን መንግሥት ተስፋ በማድረግ በመሆኑ ኑሮው ሁል ጊዜ መንገድ እንደሔደ ሰው ነው ። ጉዞውም ዘለዓለማዊውን መንግሥት ለመውረስ ነው ። በጉዞውም ወቅት በክርስቶስ ደም ፈሳሽነት የተገኘውን አዲስ ሕይወት በመመስከር በክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ የተገኘውን ድል ገና ላልሰሙት ሁሉ ማብሠር ግዴታው ነው ።

የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር ቀዋሚ ዓላማ አንድነትን ለመመሥረት ኃይሉን በቅዱስ መንፈስ ላይ አስፍሮ መጣር ነው ። በዚሁም የኅብረት ሥራው ፍጹም መዋሐድንና መስማማትን ለመጐናጸፍ ከፍ ያለ ምኞትና ተስፋ አለው ። እንደዚሁም ያለው ያንድነት ዓላማ እግዚአብሔር የሚፈቅደው ስለሆነ ፤ ከታሰበበት እውነተኛ ግብ ማድረስ ብዙ አያስቸግርም ።

ባሁኑ ጊዜ ቤተ ክርስቲያንን ብዙዎች ችግሮች ገጥመዋታል ። ይኸውም በዚህ ኻያኛ ክፍል ዘመን የሰው ልጆች በተግባረ እድ ፤ በፍልስፍናና በሳይንስም ረገድ ሆነ በመሳሰሉት ይዞታዎች ሁሉ ማዙሩን ነገር አልፈው ወደረቂቁ ዓለም በመምጠቅ ላይ ይገኛሉ ። በዚህም ጊዜ ጥያቄው የቤተ ክርስቲያን ስራት የዘመኑን የጉዞ ለውጥ ተገንዝበውታል ወይ ? የሚል ነው ።

በዚህ በምንኖርበት ዓለም ላይ በማንኛውም መሥመር መምህሩ ከደቀ መዛሙሩ ያነሰ ዕውቀት ሲኖረው በጣም አሳፋሪ ነገር ነው ።


አሁን ቤተ ክርስቲያንን የገጠማት ታላቅ ችግር ይህ ዓይነቱ ጉዳይ ነው። የሰው ልጆች አምልኮታቸው የተለያየ ይሁን እንጂ ያለ ሃይማኖት ኑረው አያውቁም ። ግን በዓለም ላይ እውነተኛው ሃይማኖት በክርስቶስ ከተመሠረተ ወዲህ ይህን ታላቅ ሕይወት የሚሰጥ እምነት ለሌሎች ያለማዳረሱ ጉዳይ በክርስቲያኖች ዘንድ ታላቅ ፍዳን ያስከትላል ። ክርስቶስ ሐዋርያትን አሠልጥኖ በመረቀበት ቀን የሰጣቸው መሪ ቃል «እስከ ዓለም ዳርቻ ድረስ ሒዱና ወንጌልን አስተምሩ በአብ ፤ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም አጥምቁ » የሚል ነበር ። እንግዲያውስ ይህ ትእዛዝ አሁንም እያንዳንዱን የክርስትና መምህር ይመለከተዋል ። በዚህም ሁኔታ አስቀድሞ ለዚህ ትምህርት ብቁ ሁኖ መገኘት እጅግ ያስመካል ፤ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበርም ዋና ዓላማው ክርስትናን እስከ ዓለም ዳርቻ ድረስ ማስተማር ነው ። እስከአሁንም ቢሆን በብዙ ሚሊዮን የሚቈጠሩ ኢአማንያንን አስተምሮ ወደ ክርስቶስ ሃይማኖት ለመመለስ በቅቷል ።

በ፲፱፻፸፫ ዓ. ም. በአፕሳላ የተሰበሰበው አራተኛ የማኅበሩ ጠቅላላ ጉባኤም አስቀድሞ ተስፋ ተጥሎበት እንደነበረው ሁሉ ከፍተኛ ሥራን አከናውኖ ለማለፍ ችሏል ። ለምሳሌ ይህ ታላቅ መንፈሳዊ ጉባኤ እያንዳንዱ አባል ቤተ ክርስቲያን ራሱን በማዘጋጀት ለታቀደው የተቀደሰ ዓላማ መልካም ፍሬን ማበርከት ይቻል ዘንድ ሁሉም በቅዱስ መንፈስ አጋርነት እንዲተባበር በማለት በጥብቅ አሳስቧል ።

በዚህ ታላቅ መንፈሳዊ ጉባኤ ተካፋይ ለመሆን ከአፍሪካ ፤ ከአውሮፓ ከእስያና ከአሜሪካ የመጡ የአብያተ ክርስቲያናት መልእክተኞችም ታላቅ የሥራ ውጤትና የመንፈስ ለውጥን ይዘው ወደየሀገራቸው እንደተመለሱ ከእያንዳንዳቸው የቃል ገለጻና ከፊታቸው ላይ ከታየው ፈገግታ የተነሣ መረዳት ተችሏል ።



የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር ጠቅላይ ጽሕፈት ቤት ያስተዳደርና ሥራ አቋም ከዚህ ቀጥሎ የተገለጸው መሆኑን ለአንባቢዎች እንገልጻለን ።



ጥንታዊነቷ በዓለም ታሪክ ተመዝግቦ የታወቀላት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንም ከማኅበሩ መሥራች አባሎች አብያተ ክርስቲያናት አንደኛዋ ከመሆኗም በላይ አራተኛው የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር ማዕከላዊ ኮሚቴ ዐቢይ ጉባኤ በራሷ ምድር ላይ እንዲከናወን በማድረጓና የእትማማች አብያተ ክርስቲያናት መልእክተኞችን ፤ የማኅበሩን ከፍተኞች ባለሥልጣኖችና ሠራተኞችን በመናገሻ ከተማዋ በአዲስ አበባ ላይ በክብር ተቀብላ በተለመደው የእንግዳ ተቀባይነት ስጦታዋ በማስተናገዷ ፤ እጅግ በጣም ከፍ ያለ መንፈሳዊ ደስታና ኩራት ተሰምቷታል ።

እስካሁን ድረስ የዓለም አብያተ ክርስቲያናትን ማኅበር ይዞታ በሩቁ ሁና ስትመለከት የነበረችው የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያንም ከጊዜ ወደጊዜ የማኅበሩን ዓላማ ጠቃሚነት በሚያከናውናቸው ሥራዎች ውጤት ስሜቷ ስለተሳበ ፤ እነሆ በቅርቡ (በ፲፱፻፹፫ ዓ. ም.) አዲስ አበባ ከተማ ላይ በተደረገው የማዕከላዊ ኮሚቴ አራተኛ ዐቢይ ጉባኤ ላይ እስካሁን ገለልተኛ ሁና የቆየችባቸውን ውስጣዊ ችግሮች ወይም ምክንያቶች በጽሑፍ በማስረዳት መልእክተኛዋን በተመልካችነት ደረጃ ስለላከች ፤ በጥናቷ ውጤት መሠረት ወደፊት ብዙ ጊዜ እንዳለፈው ሳትወስድ የማኅበሩ ቀዋሚ አባል እንደምትሆን ከፍ ያለ ተስፋ የተጣለበት ምልክትን በማሳየቷ ለአባል አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ከፍ ያለ ደስታ ተሰምቷቸዋል ።

ከዚህም በቀር በልዩ ልዩ ምክንያቶች እስካሁን ድረስ ራሳቸውን ሳይችሉ የቆዩት በአፍሪካ ፤ በእስያና በላቲን አሜሪካ ያሉ አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ በቅርቡ ራሳቸውን እየቻሉ ወደማኅበሩ አባልነት እንደሚገቡ ይታመናል ። ለጊዜው የአባል አብያተ ክርስቲያናት ቊጥር ከ፪፻፳፭ በላይ የደረሰ በመሆኑ ይህ ዓይነት የማደግ ይዞታ የማኅበሩን አቋም ጠቃሚነት በግልጽ ያስረዳል ።

መንክር ተድላ

# የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር ማዕከላዊ ኮሚቴ ስብሰባ በኢትዮጵያ

ሰው ሠራሽ ልማድን ወይሃይማኖት በማስጠጋት በማሳበብ ፣ በብቸኝነትና በገለልተኛነት መኖር ራስን የሚያስችልና የሚያስመካ መስሎ የሚታይበት ጊዜ አልፎ አብሮ በማሰብና አብሮ በመሥራት ፤ አብሮ የመኖር ፍላጎት ከሰፈነበት ዐረፍተ ዘመን ላይ መድረሳችን ምሥጢር አይደለም ። ተአምርም አይደለም ። ወይም ድንገት ሳይታሰብ የደረሰ የድንገተኛ አጋጣሚ ጉዳይ አይደለም ።

እንዴት ? ቢባል ማኅበራዊ ኑሮ ከጥንት ከመሠረት የሰው ዘር ሁሉ ከአለመኖር ወደመኖር መምጣት ከጀመረበት ከተፈጥሮ ሕግ ጋር ተጣምሮ ከዘንት ዓለም ሲያያዝ የመጣ ቋሚ ሥርዓት ነው ። በብቸኝነት ለመኖር ብቻውን የተፈጠረ ከሰው ዘር ወገን አይገኝምና ።

ዳሩ ግን የሰው ዘር ሁሉ እንደመልኩ ጠባዩና አስተሳሰቡ የተለያየ ከመሆኑ የተነሣ ፤ በጐሣ ፤ በቋንቋና በሃይማኖት እየተመካኘ በአንዳንድ ዓይነት ወፍዘራሽ ልማድ ተለያይቶ የመኖር የግለኝነት ጠባይ ብዙዎችን ወገኖች ወደርስበርስ ጦርነትና ፍጻሜ ወደማይገኝለት እልቂት ሲመራ መኖሩ አይካድም ።

በዚህም ምክንያት ብቸኛነት የፈጠረው የኑሮ ደንቃራ ብቸኛነት ያመጣው ድኅነትና ድንቊርና ፤ ብቸኛነት ያስከተለው ድካምና ጣር ጋር ፤ ብቸኝነት ያከበደው የኑሮ ቀምበር ተፅዕኖ ብዙዎችን ሲያስመርር ኖረ ። ይህኑ ለመቋቋምና የኑሮን ፈተና ለማለፍ ጥንታዊውን የተፈጥሮ አንድነትና ኅብረት በመመሥረት አብሮ የመኖር ምኞትና አሳብ ተወለደ ። ዕውቀትን ፤ ሀብትንና ጉልበትንም የማስተባበር ምሥጢር ተገለጠ ።

ይህም የአንድነት መንፈስ መጀመሪያ በቤተሰብ ተወጥኖ በኅብረተ ሰብአዊ ደረጃ እያደገ ወደአህጉር አቀፍና ወደ ዓለም አቀፍ ደረጃ ለመሸጋገር የብዙሺህ ዘመናትን ኀልፈት ጠይቋል ። ለዚህም በተለይ በመንፈሳዊው ዓለም በኩል ግምባር ቀደም ሆኖ የተገኘው የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር ነው ።

የ፴፰ ዓመት ዕድሜ ያለው ይህ ማኅበር ከተቋቋመበት ጊዜ አንሥቶ እስካሁን ድረስ ባለው ጊዜ የ፫፻፴፫ አባል አብያተ ክርስቲያናት ማዕከላዊ አስተባባሪ ድርጅት ለመሆን በቅቷል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንም የዚሁ ታላቅ ድርጅት መሥራች ከነበሩት ነባር ማኅበርተኞች አንዷ ናት ። በዚሁ ሳቢያ ነው

የማኅበሩ ማዕከላዊ ኮሚቴ ስብሰባ ከጥር ፪—፲፩ ቀን ፲፱፻፷፫ ዓ. ም. በአዲስ አበባ ሊደረግ የቻለው ፤ ማዕከላዊ ኮሚቴ የሚባለው ከጠቅላላው የአብያተ ክርስቲያናት ማኅበር የሥራ ድርጅቶች ዋናው ክፍል ሲሆን ፤ የጠቅላላው የማኅበሩ የሥራው ፕሮግራሞች የማዘጋጀትና በየጊዜውም ከአራት እስከ አምስትና ስድስት ዓመታት ባለው ጊዜ ውስጥ በሚያደርገው ስብሰባ ቤተ ክርስቲያን የሚገጥሚትን ዋና ዋና ችግሮች እየመረመረ በማጥናት ውሳኔ ለመስጠት የሚችል ነው ።

እንግዲህ ይህ የማዕከላዊ ኮሚቴ ስብሰባ በአዲስ አበባ መደረጉ ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ምን ጥቅም ሰጠ ? ብለን እንጠይቅ ይሆናል ። ተገቢ ጥያቄ ነው ። መልሱም ከሙሉ በከፊሉ እንደሚከተለው ይብራራል ።

## ያስገኘው ጥቅምና ውጤት

ክፍል ፩ ።

የዚህ ታላቅ የአብያተ ክርስቲያናት ድርጅት ማዕከላዊ ኮሚቴ ስብሰባ በአዲስ አበባ መደረጉ ለሀገሪቱም ሆነ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ታላቅ በረከት ነው ። ይኸውም ፤

፩ኛ/ አገራችን ኢትዮጵያ ጥንታዊት የክርስቲያን ደሴት እንደመሆኗ ከ፲፮፻ ዘመናት በላይ ተከባክባ ያቆየችውን የሥራና የታሪክ ቅርስ (ከ፲፮፻፶ በላይ ብዛት ያላቸው) የኮሚቴው አባሎችና በጋዜጠኛነትና በተመልካችነትም በጉባኤው ላይ ተገኝተው የነበሩት በጆሮአቸው የሰሙትንና በመጻሕፍትም ያነበቡትን ሁሉ ፤ በዓይናቸው ዓይተው ፤ በእጃቸው ዳስሰው በመረዳት በጥንታዊ ሥልጣኔና በመንፈሳዊ (ሃይማኖታዊ) እርምጃ ለመላው አፍሪቃ አህጉር የመንፈሳዊና የሥጋዊ ነፃነት ኮከብ መሆኗን እንዲመሰክሩላት ይህ ጉባኤ መልካም አጋጣሚ ሆኗል ። ኢትዮጵያ በተለይም የራሷ ምርጥ ባህልና የተቀደሰ ልማድ ያላት በሥርዓተ እምነትና በጠቅላላው የአኗኗር መልክ ከሌሎች አህጉር ሕዝብ በመተለይታ የምትታወቅበት ምልክት ያላት እውነተኛ የክርስቲያን ደሴት በመሆኗ በስብሰባው ላይ በተወከሉት በጠቅላላው መልእክተኞች ስትታሰብበት የምትኖርበትን ልዩ ዝና አትርፋለች ።

፪ኛ/ ከሚቴው በአዲስ አበባው ጉባኤ ላይ ከተነጋገረባቸው ዋና ዋና አርእስተ ጉዳዮች አንዱ ክፍል ቤተ ክርስቲያን ከልማት ተግባር ጋራ መራመድ እንደሚገባት የሚያመለክት ስለነበር ፣ ቤተ ክርስቲያናችን በዚሁ ዘመናዊ የልማት እርምጃ ተሳታፊና ተባባሪ እንድትሆን ይረዳት ዘንድ ከማኅበሩ በርከት ያለ የገንዘብ ስጦታ በርዳታ መልክ ለማግኘት እንድትችል ሆኗል ። ይኸውም ከዚህ በፊት በዝዋይ ደሴት አካባቢ ለተቋቋመው የቀሳውስት ማሠልጠኛ ትምህርት ቤትና ለመሳሰለውም አንዳንድ መንፈሳዊ ተግባር ለማከናወን ይረዳ ዘንድ ከተደረገው ስጦታ ሌላ ነው ።

፫ኛ/ ለብዙዎች መንፈሳውያን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ደቀ መዛሙርት የነፃ ትምህርት ዕድል (እስኮላርሽፕ) እንዲሰጥ ከብዙዎቹ የማኅበሩ አባል ድርጅቶች መልእክተኞች በግል ሲጠየቁ በሰጡት (መልስ) አስተያየት ሙሉ ፈቃደኞች መሆናቸውን አረጋግጠዋል ።

፬ኛ/ መንፈሳዊ ድርጅቶችን ለማቋቋምና የልማት ተግባሮችንም ስለማስተ፡፡በር ልዩ ልዩ ዘዴ በነፃ አስተሳሰብ መንፈስ ማስጠናት የሚችሉ ብዙ ታላላቅ ዐዋቂዎች በስብሰባው ላይ ስለተገኙ ፤ ከንግግራቸውና ከምክራቸው ብዙ ጥበብ ለመቅሰም አስችሏል ።

፭ኛ/ በሕዝባዊ ጥቅም በኩል ደግሞ የኮሚቴው አባሎች በአዲስ አበባ ከተማና በአካባቢዋ ባሉት አድባራት፤እንዲሁም በየገበያውና በልዩ ልዩ ሥፍራዎች ሲዘዋወሩ በሀገር ውስጥ የተሠሩ ንዋየ ቅድሳትና አልባሳት ፤ እንዲሁም መ[illegible]ቀልና ሥዕል የመሳሰሉትን ከዚህም ሌላ የሀገር ልብሶችንና የመሳሰሉትንም በውድ ዋጋ በመግዛት ለአቅራቢዎች ከፍ ያለ ገቢ አስገኝተዋል ።

፮ኛ/ በጠቅላላ የማኅበሩ አባሎች የአስተሳሰብና የንግግር መልካም ምሳሌነትና የሰውን ዘር ወዳድነት ፤(ፍቅረ ቢጽ) ታላቅ የሞራል ድጋፍ የሚሰጥ በመሆኑ ከእንግዲህ ወዲህ በብቸኛነት መኖር ሥርየት የማይገኝለት እርግማን መሆኑን አመልክቷል ።

## ጠቅላላ የጉባኤው ዓላማ በተስተካከለ ሁኔታ መፈጸም

ክ ፍ ል ፪

አዲስ አበባ ውስጥ በሚገኘው በአፍሪቃ አንድነት ድርጅት አዳራሽ ለ፲፩ ቀናት ያህል የሰነበተው ይህ የማዕከላዊ ኮሚቴ ስብሰባ ከዚህ በፊት በልዩ አህጉር ከአደረጋቸው ስብሰባዎች የሚለይበትና የሚደነቅበት ብዙ ምክንያት አለው ። ይኸውም ፤

፩ኛ/ ይህም የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር ፍጹም ዓለም አቀፍ (ኢንተርናሺናል) ድርጅት እንዲሆንና ሁሉን የሚያስተባብር ዓለም አቀፍ

አቋም እንዲኖረው አንዳንድ የሕግ አንቀጾች በማሻሻል አዲስ አንቀጽ ሊጨመሩ የሚችሉበትን ዘዴ ለማጥናት ሲመከር ብዙ ውዝግብ ያስነሣ የነበረው አስተሳሰብ መልካም አጋጣሚ ሆኖ በአዲስ አበባው ጉባኤ መፈጸሙ ተነግሯል ። ከዚህም የተነሣ በክርስትና ሃይማኖት ከሚመሩት ብቻ ሳይሆን ከልዩ ልዩ የሃይማኖት ድርጅቶች ጋር ሁሉ የቅርብ ውይይት እንዲጀመር የሚያበረታታ አስተያየት ተሰንዝሯል ።

፪ኛ/ የብዙ ሚሊዮን ሕዝበ ክርስቲያን ኃላፊነት ያለባት የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን እንኳ የማኅበሩን ዓላማ በሚገባ አጥንታ ከአምስት ዓመት በኋላ ፤ ቋሚ አባል ለመሆን ያላትን ምኞት በተመልካችነት የጉባኤው ተካፋዮች በነበሩት ወኪሎቿ አማካይነት ገልጣለች ። እስከአሁን ድረስ ግን የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን አባሎች በተመልካችነት እንጂ ፤ በቋሚ ማኅበርተኛነት አሌ ተመዘገቡም ። በአዲስ አበባው ጉባኤ ፲፫ አብያተ ክርስቲያናት ቋሚ ማኅበርተኞች በመሆናቸው ፤ የማኅበሩን አባል ድርጅቶችም ቊጥር ከ፪፻፳፭ ወደ ፪፻፴፰ ከፍ አድርገውታል ።

፫ኛ/ ዓለም አቀፍ ዜና ሆኖ የሰነበተው አንዱ ውሳኔ ነፃ ባልወጡት የአፍሪቃ አህጉር በባርነት የሚኖሩ የነፃነት ተዋጊዎችን በገንዘብም ሆነ በትምህርት መርዳት የሚቻልበትን ዘዴ የማዘጋጀቱ ጉዳይ ነበር ። ይህ አሳብ ከፍ ያለ ክርክር አስነሥቶ እንደነበር ይነገራል ። በመጨረሻው ግን ክርስቶስ ራሱ ስለሰው ልጆች መብትና ነፃነት ያሳየው የመሥዋዕትነት አርአያነት እየተጠቀሰ ሲተነተን ቆይቶ በቂ የድምፅ ድጋፍ ለማግኘት ችሏል ።

ስለዚህም ለጊዜው ከግማሽ ሚሊዮን በላይ የአሜሪካ ዶላር ርዳታ የተሰነዘረ ሲሆን ፤ ለወደፊቱም በበለጠ ሁኔታ እንደሚቀጥል ተስፋ ተጥሎበታል ።

እንዲሁም በፈረንሳይ አገር የሚገኙ ክርስቲያኖች መንግሥታቸውን በማግባባት በዘር መድልዎ ለሚመራው ለደቡብ አፍሪቃ የነጮች መንግሥት የጦር መሣሪያ መሸጡን እንዲታገድ ያደርጉ ዘንድ ተጠይቀው ለእንግሊዝ ጠቅላይ ሚኒስትር ዊልሰንና ለፈረንሣይ መንግሥት ቴሌግራም ተላልፏል ።

በተለይም ማኅበሩ የነፃነት ተዋጊዎችንና ስደተኞችን በገንዘብና በመሰለውም ማቴሪያል መርዳት ብቻ ሳይሆን ፤ የዘር መድልዎ የሚያደርጉ ጨቋኞች የመንግሥታት መሪዎችንም በክርስቲያናዊ ትምህርት በማግባባትና በማለሳለስ ሰብአዊ ርኅራኄ ያድርባቸው ዘንድ ለማግባባት የሚቻልበትን ዘዴ ሁሉ ማጥናት የኮሚቴው ዋና ዓላማ ሆኗል ።



በአጠቃላይ አነጋገር ክርስቶስ ለሰው ልጆች መብትና የነፃነት እኩልነት ያሳየው መልካም ምሳሌነት በዚህ በአዲስ አበባው ስብሰባ ላይ ጐልቶ መታየቱ መላውን ዓለም ሳያስደንቅ አላለፈም ። የዚህ ጉባኤ መከናወን የሚከፋና የማይደሰቱ ቢኖሩ እነዚያው በሰው ዘር ቆዳ ልዩነት የሚያመልኩ የዘሙኑ ግብዞች ብቻ ናቸው ። ሁኔታውም ነፃነት ወዳዶችና ለሀገር ክብር ተጋዳዮች የሆኑት ኢትዮጵያውያን ጀግኖች አርበኞች ማለት ጥንታውያንና የአሁኑም የ፳ኛው መቶ ዓመት ጀግኖች ሁሉ የፈጸሙትን የመሥዋዕትነትን ጀብዱ የሚያስታውስና የጀግንነት ወኔ የሚቀሰቅሱና ነፃ ያልወጡትን ሕዝቦች ለመርዳት የገንዘብም ሆነ የኃይል መንገዳቸውን ያጠነክሩ ዘንድ የሚያነቃቃ የመንፈስ ትንሣኤ ሆኖ የሚታሰብ ነው ።

በመጨረሻውም ልናስታውሰው የሚገባ ፤ ይህ ሁሉ የጉባኤው ውጤት ፤ አንድነት ተደምሮ ለሀገራችንና ለቤተ ክርስቲያናችን ፤ እንዲሁም ለዓለም አቀፍ ድርጅቶች ስብሳቢዎች መዲና ለሆነችው የአዲስ አበባ ከተማችን ታላቅ መታሰቢያነት ያለው የታሪክ ሐውልት መሆኑን አለመዘንጋት ነው ።

የዓለም አብያተ ክርስቲያናት አንድነት ድርጅት ለዘለዓለም ይኑር ።

አ ሜ ን ።

ቀሲስ መክብብ አጥናው ።